

# የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል



# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ

# 4ኛ ክፍል


አዘጋጆች ፡-

1. አየለ መሎሬ (ኤም.ኤ)
2. መስከረም አበራ (ኤም.ኤ)
3. ሰናይት ኃ/ሚካኤል (ድግሪ)

# የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ

# 4ኛ ክፍል


**አዘጋጆች ፡-**

1. አየለ መሎሬ (ኤም.ኤ)
2. መስከረም አበራ (ኤም.ኤ)
3. ሰናይት ኃ/ሚካኤል (ድግሪ)

**አርታኢ ፡ -** እስከዳር ገበያው (ኤም. ኤ)

**የጥራት ተቆጣጣሪ ፡-**

1. እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)
2. አወቀ ፀጋዬ (ኤም.ኤ)

**የማጣሪያ ንባብ ፡-** ምስራቅ ጠና (ዶ/ር)

# መግቢያ

ይህ የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህር መምሪያ መጽሐፍ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራኖች የተዘጋጀ መጽሀፍ ነው፡፡ ለዝግጅቱ መነሻ የሆነው እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀውን የመማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ ይህም መምህሩ የማዳመጥ ፣መናገር ፣ማንበብና መጻፍ እንዴት ማስተማር እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡ መምህሩ ተማሪዎቹን በሚያተምርበት ጊዜ እነዚህን የቋንቋ ትምህርት ክሂሎችን በየደረጃቸው ተግባራቱን ተከትሎ እንዴት ማስተማር እንዳለበት ያሳያል፡፡

መምህራኖቹ ተማሪዎቹን በሚያስተምሩበት ጊዜ አዳዲስ ጉዳዮችን፣ ገጠመኞችንና ልምዶችንም በማካፈል እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ ጥቆማ ይሰጣል፡፡

መምህራኖች ለተማሪዎች ሥዕሎችን በማስመልከት (በማሳየት) ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማስደመጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ፡፡ መምህራኖች ለተማሪዎች የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ታሪክ ወይም ምንባብ በማንበብ (በማስደመጥ) ያዳመጡትን ታሪክ ወይም ምንባብ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ በግልጽ ቋንቋ እንዲናገሩና እንዲጽፉ በማድረግ እንዴት ማስተማር እንዳለበት ጥቆማ ይሰጣል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ መምህራኖች ለተማሪዎች የመናገርና የመጻፍ ተደጋጋሚ ልምምድ እንዴት መተግበር እንዳለበት ጥቆማ ይሰጣል፡፡ በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሠረቱ አረፍተ ነገሮችን ያስነብባሉ፡፡ ይህን በማጤን የማስተማር ተግባራትን ይከውናል፡፡ ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውንም ለማሳደግ በንግግርና በጽሁፍ ሀሳባቸውን በአግባቡ እንዲገልጹ ተማሪዎችን ከተለያዩ ቃላት ጋር ማስተዋወቅ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ መምህራኖች የተለያዩ ተረቶችንና ሌሎች ጽሁፎችን በማንበብና ተማሪዎችንም በማስነበብ መረዳት ይችሉ ዘንድ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተደጋጋሚ እንዴት ማሰራት እንደሚችል ጥቆማ ይሰጣል፡፡ በአጠቃላይ የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ መምህራኖች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያሉትን የቋንቋ ክሂሎችን እንዴትና በምን አይነት ሁኔታ የትምህርቱ ይዘት በሚፈቅደው ልክ ክሂሎችን እና ቃላትን አቀናጅቶ ማስተማር እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ በተጨማሪም የስነጽሁፍን እና ሰዋስውን በትምህርቱ ይዘት ውስጥ አካቶ እንዴት ማስተማር እንደሚችል ፍንጭ የሚሰጥ ሲሆን እንዲሁም በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ካሉት መልመጃዎች ውስጥ በናሙናነት ለተመረጡት መልሳቸው ቀርቦበታል፡፡ የመመዘኛ ተግባራትም ተካተዋል፡፡

## ማውጫ ገጽ


ምዕራፍ አንድ ፡- የቤትና የዱር እንስሳት-----------------------------6

ምዕራፍ ሁለት፡- ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳት--------------------------21

ምዕራፍ ሶስት፡- የቤት ውስጥ መገልገያዎች--------------------------36

ምዕራፍ አራት፡- የንጽህና አጠባበቅ-------------------------------------45

ምዕራፍ አምስት፡-መጓጓዣ----------------------------------------------62

ምዕራፍ ስድስት፡- የምግብ አይነትና አዘገጃጀት-----------------------74

ምዕራፍ ሰባት፡-የሙዚቃ መሳሪያዎች----------------------------------83

ምዕራፍ ስምንት፡- ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎች-------------------97

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- አካባቢያችን-----------------------------------------111

ምዕራፍ አስር፡- ተረት-------------------------------------------------125

# ምዕራፍ አንድ

# የቤትና የዱር እንስሳት

(ክፍለ ጊዜያት 16)

**የምዕራፉ አላማዎች ፡-**

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ፡-

- የተለያዩ የቤትና የዱር እንስሳት ስሞችን ይዘረዝራሉ፡፡
- እንስሳቱ እራሳቸውን ከጠላቶቻቸው የሚከላከሉባቸውን መንገዶች ይናገራሉ ፡፡
- እንስሳቱ ለሰው ልጆች የሚሰጡትን ጥቅም ይገልጻሉ፡፡
- ትዕዛዞችን ተከትለው መልመጃዎችን ይሰራሉ፡፡
- በተገቢው መልኩ ፊደላትን ያነባሉ፡፡
- ዲቃላ (ድርብ) ሆሄያትን ታነባላችሁ፣ትጽፋላችሁ
- በተነባቢ የእጅ ፅሁፍ ቃላትንና አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መስመር ጠብቀው ይፅፋሉ ፡፡
- ከሠንጠረዥ ውስጥ በሆሄያት ቃላትን ይመሠርታሉ፡፡

## አዳምጦ መናገር

## አንደኛ ሳምንት፡-    ትምህርት አንድ

### የቤትና የዱር እንስሳት ስሞችን አዳምጦ መናገር

መምህር/ት መጽሐፉ የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳትና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በሚያዳብር መልኩ የተደራጀ ነው በመሆኑም እርስዎ ተጨማሪ መልመጃዎችን ሲያዘጋጁ ክሂሎቹን በቅንጅት ማስተማርና ማዳበር በሚችል መልኩ ቢሆን ይመረጣል።

**ይህን ክፍል ማስተማር ሲጀምሩ ፡-**

እንደየ አካባቢያቸው ሁኔታ ተማሪዎቹ የሚያውቋቸውን የቤትና የዱር እንስሳት ስያሜዎችን እንዲጠሩ ያድርጓቸው። የቤትና የዱር እንስሳትን ልዩነት እና ጥቅማቸውን ዘርዝረው እንዲገልጹ ያድርጉ። ይህም ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ዕለቱ የትምህርት ይዘት ከመግባታቸው በፊት የቀደመ ዳራዊ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስ ያግዛል። የዕለቱን የትምህርት ይዘት በተነቃቃ መንፈስ እንዲከታተሉ ያደርጋል።

**የሚከተሉትን የቤትና የዱር እንስሳት ስሞች ሰሌዳ ላይ ይጻፉ።**

| | |
|---|---|
| 1.ድመት | 5.ቀጭኔ |
| 2.አንበሳ | 6.ጉማሬ |
| 3.አውራ ዶሮ | 7.ፈረስ |
| 4.ነብር | 8.ጃርት |

መምህር/ት ፡- በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን የእንስሳት ሥዕል እያሳዩ ሰሌዳ ላይ ከጻፏቸው ቃላት ስያሜያቸውን እየወሰዱ በየስዕሉ ጎን በመጻፍ ያንብቡላቸው ፡፡

ሲነበብ ያዳመጡትን የእንስሳት ስሞች ተማሪዎቹ ተራ በተራ እንዲጠሯቸው በማድረግ በትክክል መጥራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

በመቀጠል መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡ ሲያሰሩ የእንስሳቱን መጠሪያ ስም ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡

የእያንዳንዱን እንስሳ ስዕል እያሳዩ በምሳሌው መሠረት በቃል እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎች ለጥያቄው ተገቢውን መልስ እንዲሰጡ ያበረቷቷቸው፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት ሁለት

### መናገር

### ምስሎችን ተመልክቶ ጠላቶቻቸውን የሚከላከሉበትን መንገድ መግለጽ

በዚህ ክፍልም ከላይ የተከተልነውን የማስተማር ዘዴ የሚከተሉት ተግባራት ቀርበዋል፡፡ የእያንዳንዱን እንስሳ ስዕል እያሳዩ ጠላቱን ለመከላከል የሚጠቀምበትን ዘዴ በምሳሌው መሠረት በቃል እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው፡፡

ተማሪዎቹ ተጠይቀው የሚሰጡትን ምላሽ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ መልሱን የሚናገሩ ተማሪዎችን "ጎበዝ" በማለት ያበረታቷቸው፡፡

የሌሎችንም እንስሳት ስሞች በማቅረብ በንባብ ያስደምጧቸው። በተማሪ መጽሐፍ ከ1-5 የቀረቡትን የእንስሳት ስዕሎች እንዲያዩ ያድርጓቸው። ስማቸውን (አዞ፣ ጅብ፣ ፈረስ፣ ኤሊ፣ እባብ ) በማለት ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው።

ተማሪዎች የእያንዳንዱን እንስሳት ስም እየተመለከቱ ጠላቶቻቸውን የሚከላከሉበትን ዘዴ በቡድን ይወያዩባቸው።

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት ሶስት

### የአማርኛ ቋንቋ ዲቃላ(ድርብ) ሆሄያት

መምህር/ት ፡- እባክዎ የተማሪዎችን የቀድሞ ችሎታቸውን ለማወቅ የአማርኛ ሆሄያትን እንዲጠሩ ይጠይቋቸው። በቀረበው ሆሄያትም ቃላት መስርተው በቃል እንዲገልጹ ያድርጉ። ይህም ተማሪዎች ሆሄያትን ሲጠሩ እና ቃላትን መስርተው ሲጠሩ አጥርቶ የመግለጽ (የንበት) ችግሩ የቱ ጋ እንደሆነ ፍንጭ የሚሰጥ በመሆኑ መምህሩ ይህን ችግር ከመሰረቱ ለመፍታት ያስችለዋል ተብሎ ይታሰባል። ስለሆነም የመምህሩ ድጋፍና ክትትሉ የጠበቀ ይሁን።

- የሚከተሉት ድምጾች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድምጾች ተፅዕኖ ሊያርፍባቸው የሚችልባቸው ተብለው ስለሚገመቱ ድምጾቹን ሲጠሩ አዳምጠው በትክክል መልሰው መጥራት መቻላቸውን ይከታተሉ። ያረጋግጡ።

**ድምጾች፡-**

**ሲ፣ ስ፣ ሚ፣ ም**

**በ፣ ቤ፣ ብ፣ ቢ**

**ቆ፣ ቋ፣ ቃ**

**ነ፣ ኖ**

**ኘ፣ ኞ**

**ፐ፣ ፕ**

የሚከተሉትን ዲቃላ(ድርብ) ሆሄያት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉና ያስቆጥሯቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሏ | ሟ | ሯ | ሷ |
| ሿ | ቋ | ቧ | ቷ |
| ቿ | ኳ | ኂ | ኗ |
| ኟ | ኋ | ዟ | ዢ |
| ጧ | ጯ | ዷ | ጇ |
| ጿ | ፏ | ጷ | |

በእነዚህ ሆሄያት መነሻነት በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን መልመጃ እንዲሠሩ ይርዷቸው፡፡

## ማስታወሻ

የደቡብ ክልል 55 ብሔረሰቦችን ያቀፈ ክልል እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ብሔረሰብ የየራሱ ቋንቋ አለው ። በመሆኑም ተማሪዎቹ በተለያየ ቋንቋ አፋቸውን በመፍታታቸው ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ወይም በማህበራዊ መስተጋብር ጊዜ በድምጽና በጽሕፈት ተፅዕኖ ሲያሳድር ይስተዋላል፡፡ እነዚህን ስህተቶች ተፈጥሯዊ መሆናቸውን እንዲረዱና በበጎ ጎናቸው እንዲያዩ ማድረግ ይገባል፡፡

ለምሳሌ ያህል፡- **ቋንቋ** ብሎ ለመጥራት **ቆንቃ** ብለው ያሚያነቡ፣ **ሰኞ** ብለው ለመጥራት ‹‹ሰኖ››በማለት ‹‹ኝ›› ድምጽን ለመጥራት የሚቸገሩ አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ‹‹ ፍራፍሬ ›› የሚለውን ቃል ፕራፕሬ ብለው ይጠራሉ፡፡ ‹‹ ድምጽ›› ለማለት ‹‹ ድምጥ›› የሚሉም ያጋጥማሉ፡፡

ሌላው ችግር ደግሞ ግዕዝና ሳልስ ድምጾችን ለይቶ ያለመጥራት ችግር ነው፡፡ ‹‹በለጠ›› ለማለት ‹‹በላጣ›› ወይም ‹‹በለጣ›› ‹‹አየለ›› ለማለት ‹‹አያላ›› የሚሉ አሉ፡፡

ሲጽፉ ደግሞ ‹‹ በቀለ›› ለማለት በቀሌ ፣በለጤ እያሉ የሚጽፉም አሉ፡፡ ይህንን ስህተት በተቻለ መጠን ለመቀነስ መምህራን እንደየ አካባቢያቸው የድምጾችን አጠራር በመከታተልና ጽሑፍ አጣጣላቸውንም በማየት ሊያስተካክሉ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ዲቃላሆሄያትን በቀላሉ ስለማይለምዷቸው መምህራኑ እየጠሩ እያስደመጡ ቢያለማምዷቸው የተሻለ ይሆናል፡፡

ማንበብ

## ትምህርት አራት

### የእንስሳትን ስም ማንበብ

መምህር/ት የእንስሳ ስሞች የተጻፈባቸውን ፍላሽ ካርዶችን ያዘጋጁና ለተማሪዎች በማሳየት ተራ በተራ እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ ማንበብ የቻለውን ተማሪ በማበረታታት ያነበበውን የእንስሳ ስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያስጨብጭቡለትና ደጋግሞ ለተማሪዎች እንዲያነብ ያድርጉት፡፡ ሂደቱ ሌሎች ተማሪዎችንም ስለሚያነሳሳና ስለሚያነቃቃ ይደጋግሙት፡፡ ሌላ የተሻለ አማራጭ መጠቀምንም አይርሱ፡፡

በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ መልመጃ አንድ ስር የቀረቡትን ስሞች እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

የቤትና የዱር እንስሳትን ስሞች ቀላቅለው በመጻፍ፣ የቤት እንስሳትንና የዱር እንስሳትንም ስሞች ለየብቻ መድበው ጽፈው ሲያነቡ በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ መልመጃ ሁለት ስር የቀረቡትን አጫጭር ዓ.ነገሮች በደብተራቸው ገልብጠው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ዲቃላ ድምጾቹን በትክክል ላነበቡ  ተማሪዎች ያበረታቷቸው ያነበቡትን አረፍተ ነገር በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ደጋግመው እንዲያነቡና ለተማሪዎች አርአያ እንዲሆኑ ይርዷቸው፡፡

መምህር/ት ፡- በዚህ ክፍለ ትምህርት በተለይ መልመጃ ሶስት ቃላትን ማንበብና ትርጉማቸውን ማግኘት ነው፡፡ ይህን መልመጃ በቤት ሥራ መልክ በመስጠት ወላጆችን ጠይቀው ወይም መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው ትርጉማቸውን ጽፈው መጥተው ክፍል ውስጥ ቢያነቡ አንዱ ከሌላው ሊማማርበት ይችላል፡፡

## ትምህርት አምስት

### አረፍተ ነገር መስርቶ ማንበብ

መምህር/ት፣ በትምህርት አምስት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ ተማሪዎች **ሁለት ክሂሎችን** ይተገብራሉ፡፡ የመጀመሪያው በቃላት አረፍተ ነገር መመስረት ሲሆን በመቀጠል የመሠረቱትን አረፍተ ነገር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ቋንቋውን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስለሚማሩ ረጃጅም አረፍተ ነገሮችን መመስረትም ሆነ ማንበብ ሊከብዳቸው ይችላል፡፡ እርስዎ ባለ ሁለትና ባለ ሶስት ቃል አረፍተ ነገር እየመሠረቱ ለምሳሌ (አንበሳ ይናከሳል፡፡ እባብ ይናደፋል፡፡ ላም ወተት ትሰጣለች ፣ ወዘተ) እያሉ አቅጣጫ ያሳዩዋቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት

### ምንባብ

#### ማስታወሻ

ንባብ ለማስተማር በቅድሚያ የሚነሱ 3 ጥያቄዎች አሉ፡፡

የመጀመሪያው ፡- የማነበው ምንድን ነው?

ሁለተኛው፡- የማነበው ለምንድን ነው ?

ሶስተኛው፡- የማነበው እንዴት ነው?

የሚሉት ይገኙበታል፡፡ በዚህ ደረጃ ንባብ የሚጀምረው ድምጾችን በመቁጠር ነው፡፡ በዚህ መሠረት መምህሯ/ሩ የድምጾች ቅንጅት የሚፈጥራቸውን ቃላት በማስቆጠርና እንደገና በአንድ ላይ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን ያለማምዷቸው፡፡

ንባብ በዕድሜ ተወስኖ በዕውቀት ተመጥኖ የሚተገበር ክሂል ነው፡፡ ስለዚህ ህፃናት ማንበብ ያለባቸው በዕድሜያቸውና በዕውቀት ደረጃቸው መጠን ስለሆነ ለተማሪዎች የሚያነቡትን ሲመርጡ የንባብ ፍቅራቸውን የሚጨምር ይዘት ያለው እንዲሆን ያድርጉ፡፡

◈መምህራኖች፡- በዚህ ክፍል የቀረበው ተረት ዳኛው ሌባን ለመያዝ (ለማግኘት) የተጠቀመበትን ብልሃት የሚያሳይ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ሌብነት ማህበረሰብ ውስጥ የተወገዘ መሆኑን ከማሳየት ባሻገር ሌባ ሊያዝ እንደሚችልም የሚጠቁም ነው፡፡ ተረቱን በፍጥነት ለማንበብ የተማሪዎች ዕድሜ የትምህርት ደረጃቸውም ገና ነው፡፡ ስለዚህ መምህሯ/ሩ ተማሪዎቹን ማስነበብ ከመጀመርዎ በፊት ድምጽን ከፍ አድርገው በማንበብ ሞዴል ሆነው ካስደመጡ በኋላ ማንበብ

ያስጀምሯቸው፡፡ ከማንበብዎ በፊት ግን ለትግበራ ማስጀመሪያ የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ሁሉም ተማሪዎች እንዲነቃቁ ማድረግ፡፡ ይህም የምንባቡን መልዕክት እንዲገሚቱ ስለሚያደርግ የተሻለ ዘዴ ይሆናል፡፡ ከዚህ የተሻለ ዘዴ ካለም መጠቀም ይቻላል፡፡ በመቀጠልም መልመጃ አንድን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ትምህርት ሰባት፡-**

**የእንስሳትን ምድቦች ማንበብ**

**ወተትና ቅቤ የሚሰጡ**

**እንስሳት፡-**

- **ላም**
- **ፍየል**
- **ግመል**
- **በግ**
- **ጠላታቸውን በመናከስ የሚከላከሉ**
  - **ውሻ**
  - **ቀበሮ**
  - **ጅብ**
  - **አንበሳ**

**ጠላታቸውን በቀንዳቸው በመዋጋት የሚከላከሉ እንስሳት**

- ጎሽ
- አውራሪስ
- አጋዘን
- በሬ
- ዋልያ

መምህር/ት፡- ይህን ክፍል ከማስነበብዎ በፊት በየምድቡ ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን እንስሳት ስም እንዲጠሩ ይገፋፏቸው፡፡ የጠሯቸውን እንስሳት ስሞችና ከላይ የቀረቡትን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ በተማሪዎቹ መጽሐፍ ከቀረበው ሥዕል ጋር እንዲያስተያዩና እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

በመቀጠል ተማሪዎች መልመጃውን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ መልመጃውን ሲያሰሯቸው እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጨምረው ጽፈው ቢያስነብቡ ወይም ሌላ የተሻለ አማራጭ ካለ ቢጠቀሙ የተሻለ ይሆናል፡፡

## ትምህርት ስምንት፡-

### አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መመስረትና ማንበብ

መምህር/ት፡- ይህን ክፍል ሲያስተምሩ የቀረቡትን የቤት እንስሳ ስያሜዎችን ተጠቅመው አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መሰርተው እንዲያነቡ ተማሪዎችን ያበረታቷቸ፡፡

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን አጫጭር አረፍተ ነገሮች በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡ ያረጋግጡ፡፡

### መፃፍ

## ትምህርት ዘጠኝ

### የእንስሳትን ስም መፃፍ

መምህር/ት፡- ይህን ክፍለ ትምህርት ሲያስተምሩ፤ በመጀመሪያ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን የቤት እንስሳ ስያሜዎችን በደፍብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

መምህር/ት፡- ተማሪዎች መልመጃ አንድ ከቤትና ከዱር እንስሳት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቃላት መሰረት አድርጎ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች እነዚህን ቃላት ተጠቅመው አጫጭር አረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ይርዷቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መልመጃ ሁለትን ሲያሰሩ የቀረቡትን የእንስሳ ስያሜዎች በመጠቀም የተጓደሉ አረፍተ ነገሮችን እንዲያሟሉ ይርዷቸው፡፡

# ትምህርት አስር

### ቃላትን ማዛመድ

መምህር/ት፡- ይህን ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ከመስራታቸው በፊት ተማሪዎች የሚያውቋቸውን የእንስሳ ስሞችን በመጥራት ባህሪያቸውንም እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ቀጥሎ የሚመጣውን ተግባር በቀላሉ ለመስራት ያስችላቸዋል፡፡ በመቀጠል የአዛምድ ጥያቄውን ያሰሯቸው፡፡

መምህር/ት፡- የቀረቡትን ሆሄያት በማንበብ ለተማሪዎች በቃል መጻፍን ያለማምዷቸው፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይረዳል፡፡

| | |
|---|---|
| ከ እና አ | ፐ እና ነ |
| ጠ እና ጨ | ፀ እና ዐ |
| ፓ እና ፖ | ፐ እና ተ |
| ጸ እና ደ | ፉ እና ፋ |

በአጠቃላይ ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ መተግበሪያ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች በጥንድ፣ በቡድንና በግል በመሆን መልመጃዎችን እንዲሠሩና እንዲማሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### መርጃ መሣርያ

በቋንቋ ትምህርት ሂደት በመርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ሥዕሎች፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ

የሚሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሣርያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

**ግምገማ**

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት እንዲጽፉ በማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፤

▸ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽ ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ፡-

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን በመጠቀም መገምገም ተገቢ

## በናሙናነት የተመረጡ መልሶች

በምዕራፍ አንድ ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥና የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው:: ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም:: ይሁን እንጂ በአዳምጦ መናገር ስር የቀረቡት ምስሎችን፣ ስሞችንና የቀለሞችን አይነት በቁጥራቸው ልክ በትክክል እንዲጽፉ በማድረግ ማሰራት ይቻላል::

## አዳምጦ መናገር

### ትምህርት ሶስት

### መልመጃ አንድ የ2ኛ ጥያቄ መልስ

### የአማርኛ ቋንቋ ዲቃላ (ደርብ) ሆሄያት

| ተ.ቁ | ሆሄያት | በሆሄያቱ የተመሰረቱ ቃላት |
|---|---|---|
| 1 | ኋ | ኋዳ ፣ ኋያ ፣ ኋደኛ፣ ኋኀለ |
| 2 | ሟ | ሟሟ ፣ ሟጥ፣ሟሽሽ |
| 3 | ቧ | ቧንቧ ፣ቧረቀ ፣ቧልት |
| 4 | ቋ | ቋንቋ ፣ ቋሚ ፣ቋጣሪ፣ ቋት ፣ቋቁቻ ፣ቋር፣ |
| 5 | ጧ | ጧፍ፣ ጧሪ ፣ |

መጻፍ

## ትምህርት ዘጠኝ

### የእንስሳትን ስም መፃፍ

**መልመጃ ሁለት፡-**

1.አዞ

2. ጦጣ፣ ዝንጀሮ

3. ድመት

4. ጅብ

5. አውራ ዶሮ

## ትምህርት አስር

### ቃላትን ማዛመድ

**መልመጃ፡-**

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. ለ

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳት

**(የክፍለ ጊዜ ብዛት 16)**

**የምዕራፉ አላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-**

- ባህላዊና ዘመናዊ የልብስ ዓይነቶችን ላይተው ይዘረዝራሉ፡፡
- የለበሱት ልብስ ከምን እንደተሰራ ይናገራሉ፡፡
- የለበሱትን የልብስ ቀለም ዓይነት ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የልብስ ዓይነቶችን ከስያሜያቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- የአልባሳቱን ስያሜ ተጠቅመው አጫጭር ዐ.ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡
- የልብስ አይነቶቹ ከምን እንደተሰሩ ይናገራሉ፡፡
- ቃላትንና ዐ.ነገሮችን በተገቢው መልኩ ያነባሉ፡፡
- በተውላጠ ስሞች ዐ.ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት አንድ

### አዳምጦ መናገር

### የልብሶችን ስያሜ መናገር

መምህር/ት፡- እባክዎ የተማሪዎቹን የቀደመ ዕውቀት ለማወቅ የለበሷቸውን ልብሶች ባህላዊ ወይም ዘመናዊ ስለመሆናቸው ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያድርጓቸው፡፡

የለበሱት ልብስ ከምን እንደተሰራ የሚያውቁትን እንዲገምቱ ያነሳሷቸው፡፡ እባክዎ መምህር/ት በተማሪው መፅሃፍ ላይ ለቀረቡ ስዕሎች ስያሜያቸውን ሰሌዳ ላይ ይፃፉ፡፡

1. ጂንስ ሱሪ
2. የሀበሻ ቀሚስ
3. የቆዳ ጃኬት
4. ብርድ ልብስ
5. ጋቢ
6. ሹራብ

መምህር/ት እባክዎ በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን የአልባሳት ሥዕሎች እያሳዩ ሠሌዳ ላይ ከጻፏቸው ቃላት ስማቸውን እየወሰዱ በየቁጥሩ ትይዩ በመፃፍ ያንብቡላቸው፡፡

ያዳመጡትን የአልባሳት ስሞች በትክክል መጥራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

የአልባሳቱን አይነቶች ለይተው መናገራቸውን ያረጋግጡ፡፡

የሚከብዷቸው ስያሜዎች ካሉ ደጋግመው በመጥራት እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው፡፡

በመቀጠል መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡ መልመጃውን ሲያሰሩ በእያንዳንዱ ጥያቄ ስር የተነሳው ልብስ ከምን እንደ ተሰራ በምሳሌው መሰረት በቃል እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው፡፡

መምህር/ት እባክዎን በአካባቢያቸው ተዘውትረው የሚለበሱ ልብሶች ከምን እንደሚሰሩ እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡

የሚከተሉትን የልብስ ስሞች እያነበቡላቸው ከምን እንደተሰሩ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

መምህር/ት፡- በትምህርት አንድ መልመጃ አንድ ስር የቀረቡ ልብሶች ከምን እንደተሰሩ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት ሁለት

### ስዕሉን በማየት የልብሱን አይነት መግለጽ

መምህር/ት፡- እባኮትን የተማሪዎቹን ዳራዊ ዕውቀት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተማሪዎቹ የለበሱት ልብስ ቀለሙ ምን ዓይነት እንደሆነ ለክፍል ተማሪዎች እንዲነግሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም የተለያዩ ቀለማትን ዓይነት ቀድመው እንዲያስቡ መነሳሳትን ይፈጥርላቸዋል፡፡

መምህር/ት፡- እባኮትን በተማሪዎች መማሪያ መጽሃፍ ላይ የቀረቡትን ሥዕሎች እንዲያዩ ያድርጉ፤ የአልባሳቱን ስያሜ ከቀለሙ ዓይነት ጋር አያይዘው በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ፡፡

1. ጥቁር ሱሪ
2. ነጭ ሹራብ
3. ሰማያዊ ቀሚስ
4. ቀይ ቲሸርት
5. አረንጓዴ ጃኬት
6. ቢጫ ሸሚዝ

መምህር/ት እባኮትን በተማሪ መፅሀፍ ውስጥ ያሉትን የአልባሳት ሥዕሎች እያሳዩ ሠሌዳ ላይ ከጻፏቸው ስያሜዎችን በየተራ ቁጥሩ ትይዩ በመፃፍ ያንብቡላቸው፡፡

- አልባሳቱን ስያሜ ከቀለም ዓይነቱ ጋር አያይዘው ስለመጥራታቸው ያረጋግጡ፡፡
- የአልባሳቱን ስያሜ ከቀለም አይነቱ ጋር በትክክል ለይተው ስለማወቃቸው ይከታተሉ፡፡
- በቀረበው ምስል ውስጥ የማይታወቁ (የከበዳቸው) የልብስ ስያሜ ካለ ያንን ደጋግመው በመጥራት እንዲያርሙ፤ እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው፡፡

መምህር/ት፡- ከዚህ በመቀጠል መልመጃውን ያሰሯቸው፡፡ መልመጃውን ሲያሰሩ፤ ስለለበሱት ልብስ በጥያቄው መሰረት በትክክል መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት ሶስት

### ምስሎችን አይቶ ልብሶቹ ከምን እንደተሰሩ መናገር

መምህር/ት፤ተማሪዎች ልብስ ከምን እንደሚሠራ ሊያውቁ ስለሚገባ ይህንን የሚያስገነዝቡ ጥያቄዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ለማወቅ ትምህርት ሶስት ስር የቀረቡትን የማነቃቂያ ጥያቄዎችን በቅድሚያ ይጠይቋቸው፡፡

መምህር/ት፡- እባክዎ የሚከተሉትን የልብሶች ስያሜ ሰሌዳ ላይ ይጻፏቸው፡፡

1. ከቆዳ
2. ከጥጥ (የሀበሻ ቀሚስ)
3. (ከጥጥ) በእጅ የተሰራ የክር ሹራብ
4. ከጥጥ የተሰራ ጋቢ
5. ከጥጥ የተሰራ ረጅም ጉርድ

መምህር/ት፡- እባክዎ በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ ያሉትን ልብሶች ከምን እንደሚሰሩ ይናገሩ፡፡ የልብሶቹ ሥዕሎች በተማሪ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ስያሜያቸውን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ስያሜውን እያዩ ልብሶች የተሰሩበት ቆዳነው ወይም ጥጥ ወይም ሌላ ከሆነ እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡ እያንዳንዱ ልብስ የተሰራበትን ነገር በትክክል መጥራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት ፡- ትምህርት አራት

### አዳምጦ መናገር

የብሔር ብሔረሰብ ቀን ሲከበር እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱ መገለጫ የሆነውን ባህላዊ ልብስ ለብሶ ይወጣል ከነዚህም አንዱ የሐመር ብሔረሰብ ባህላ ልብስ ነው፡፡

### የሐመር ባህላዊ አልባሳት

የሐመር ልጆች በተለይም ሴቶች ሀፍረተ-ሥጋቸውን ለመሸፈን ሲሉ ከቆዳ የሚዘጋጅ በሐመርኛ “ሺራን” የሚባል ግልድም ያገለድማሉ፡፡ ከላይ ደረታቸውን ለመሸፈን ደግሞ የቆዳ ጥብቆ “ቃሼ” ያጠልቃሉ፡፡ ሴቶች በዕድሜ ከፍ ሲሉ ደግሞ ከፊት ለፊታቸው “ቶቆ” ከወደ መቀመጫቸው ደግሞ “ፋላንቲ” የተሰኘ ከቆዳ የሚዘጋጅ ባለጥንድ ጉርድ ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ ካገቡ በኋላ ደግሞ ከወገብ በታች ማለትም ከፊትለፊት “ኢኮርባ” ከኋላ “ቡዶኮርባ” የሚባል ከፍየል ቆዳ የተዘጋጀ ጥንድ ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ “ቃሼ” ጥብቆ ያጠልቃሉ፡፡

ምንጭ፡- በደ.ብ.ብ.ሕ. ክልላዊ መንግስት የብሔረሰቦች ምክር ቤት አርባምንች ዩኒቨርሲቲ እና የጋሞ ጎፋ ዞን ባህል፤ ቱሪዚም እና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን መምርያ፤ ገጽ 220 ፣ግንቦት 2008ዓ.ም፤ ሀዋሳ።

መምህር/ት፡- እባክዎ ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ሺራን፣ ቃሼ፣ ቶቆ፣ ፋላንቲ፣ ኢኮርባ፣ ቡዶኮርባ ለሚባሉ የመገኛ ቋንቋ ቃላት የአማርኛውን መተኪያ ቃለት ጭምር በሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው። በመቀጠል ምንባቡን ረጋ ባለ ድምጽ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። ባዳመጡት ምንባብ መሠረት መልመጃ አንድ ላይ ለቀረበው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ።

## ማስታወሻ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙብሔር ብሔረሰቦች መዲና ነች። እያንዳንዱ ብሔረሰብም የየራሱ የሆኑ መገለጫ ባህሎች አሉት። ከነዚህም አንዱ ባህላዊ አልባሳት ናቸው። ስለዚህ ተማሪዎቹ ስለሀገራቸው ባህላዊ አልባሳት ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የአንዳንድ ብሔረሰቦችን አልባሳት አይነት ተመልክተው መናገር እንዲችሉ የአልባሳቱ ፎቶዎች በተማሪ መጽሀፍ ውስጥ ቀርበዋል። ከዚያ በፊት ግን ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች አንዱ የሐመር ብሔረሰብ ባህላዊ አለባበስ ሲሆን ይህም ከሌሎች ባህላዊ ልብሶች ለየት የሚል ስለሆነ ምንባብ ውስጥ ተካቷል። ሙሉ በሙሉ ከቆዳ የተሰሩ ልብሶች የሚለብሱ ብሔረሰቦች ያሉን መሆኑንም ተማሪዎቹ ይረዱ ዘንድ ከሌሎቹ ባህላዊ ልብሶች ጋር በማነጻጸር ለተማሪዎቹ ያሳዩዋቸው።

## ሁለተኛ ሳምንት ፡- ትምህርት አምስት

### ባህላዊ አልባሳትን ለይቶ መናገር

በተማሪ መፅሃፍ ውስጥ የተለያዩ ብሔረሰቦች አልባሳት ቀርበዋል፡፡ አልባሳቱን በመመልከት ተማሪዎቹ የየትኛው ብሔረሰብ አልባሳት እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ የሁሉንም ብሔረሰብ ባህላዊ አልባሳት በዚህ መፅሀፍ ለማካተት ስለሚያዳግት የሌሎቹንም ባህላዊ አልባሳት እንደየ አካባቢያቸው በማቅረብ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያድርጓቸው፡፡

ሥዕል 1 የጋሞ ብሄረሰብ

ሥዕል 2 የጌዴኦ ብሄረሰብ

ሥዕል 3 የኮንታ ብሄረሰብ

ሥዕል 4 የሀዲያ ብሄረሰብ

ሥዕል 5 የወላይታ ብሄረሰብ

ሥዕል 6 የዳውሮ ብሄረሰብ

ሥዕል 7 የሀመር ብሄረሰብ

ሥዕል 8 የጉራጌ ብሄረሰብ

**ማንበብ**

## ትምህርት ስድስት

### የልብሶችን ስም ማንበብ

የልብስ ስሞች የተፃፉበትን ፍላሽ ካርዶችን ያዘጋጁና ለተማሪዎች በማሳየት ተራ በተራ እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ ማንበብ የቻለውን ተማሪ በማበረታታት ያነበበውን የልብስ ስም በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ ያስጨብጭቡለትና ደጋግመው ለተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ሂደቱ ሌሎቹንም ስለሚያነሳሳና ስለሚያነቃቃ ይደጋግሙት፡፡ ሌላ አማራጭ ካለም መጠቀም አይርሱ፡፡

መምህር/ት፡- በተማሪ መፅሃፍ በሀረግ መልክ የቀረቡትን የአልባሳት ስያሜዎች ተራ በተራ ያስነብቧቸው፡፡ ሲያነቡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ በትክክለኛ ንበት መጥራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

በተማሪ መፅሀፍ መልመጃ አንድ ስር የቀረቡትን ጥንድ ጥንድ ስሞች ተጠቅመው አጫጭር አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

በመቀጠልም አረፍተ ነገሮቹን ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## ትምህርት ሰባት፡-

### አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ማንበብ

የተማሪው መፅሐፍ የተደራጀው በተማሪዎቹ ዕድሜና ዕውቀት መጠን የተማሪዎቹን አዳምጦ የመረዳትና የመናገር፤ የማንበብና የመፃፍ ክህሎቶችን በሚያዳብር መልኩ ነው፡፡ ስለዚህ እርስዎ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማርና ማዳበር በሚቻል መልኩ ተጨማሪ መልመጃዎችን አዘጋጅተው ቢያስነብቡ የተሻለ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በተማሪ መፅሃፍ የቀረቡትን አጫጭር አረፍተ ነገሮች ድምጻቸውን ከፍ አደርገው ረጋ ብለው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ አንብበዉ ሲያጠናቅቁ የቀረቡትን የልብስ ስሞች በመጠቀም ዐ.ነገሮችን እንዲመሰርቱና የመሰረቱትን አረፍተ ነገሮች እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ትምህርት ስምንት

### ምንባብ

መምህር/ት፡- "አንበሳ ፈጣሪውን ይቅርታ ጠየቀ" የሚለውን ምንባብ ያስነቡቧቸው፡፡ የተማሪዎቹን የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመገመት ስለአንበሳ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያደፋፍሯቸው፡፡

በቁልፍ ቃልነት የቀረቡትን ቃላት ትርጉማቸውን በሚገባ እንዲረዱ ያድርጓቸው፡፡ ምንባቡን ሲያነቡ የማንበብ ፍጥነት ከተማሪ ተማሪ ሊለያይ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ተማሪዎች በአንድ ጊዜ በማስጀመር ይከታተሏቸው፡፡

የመጀመሪያውን አንቀፅ አንብበው ሲጨርሱ ቆም ብለው የሚቀጥለው መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ይናገሩ ፡፡

- አንብበው ለማጠናቀቅ የሚቸገሩ ከሆነ ተጨማሪ ሰዓት እንዲጠቀሙ ያድርጉ፡፡

አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ ስለ አንበሳ፣ አውራ ዶሮ፣ ዝሆን፣ ትንኝና ሌሎችም እንስሳት ግዝፈት፣ ጥንካሬና ፍጥነት እንዲሁም የሰውን ልጅ የሚጎዱና የማይጎዱ የትኞቹ እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

በመጨረሻም መልመጃ አንድና መልመጃ ሁለትን ያሰሯቸው፡፡ ለማንበብና መልመጃዎችን አጠናቆ ለመስራት ሁለት ክፍለ ጊዜ ሊፈጅ ስለሚችል በቤት ሥራ መልክ መስጠትም ይቻላል፡፡

**መፃፍ**

## ትምህርት ዘጠኝ

**የልብስ አይነቶችን ከስያሜያቸው ጋር ማዛመድ**

መምህር/ት፡- ተማሪዎች ከልብሶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቃላት እንዲያነቡና ሌሎችንም የሚያውቋቸውን ቃላት እንዲጽፉ ይርዷቸው፡፡ በመቀጠልም በመልመጃ አንድ እና በመልመጃ ሁለት ስር ያሉትን ጥያቄዎች መልስ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

## ትምህርት አሥር ፡-

### ልብሶች የሚሰሩባቸው ግብአቶች አንብቦ መፃፍ

መምህር/ት፡- እባክዎ ተማሪዎቹ የሚለብሷቸው ልብሶች ወይም በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች የሚለብሷቸው ልብሶች ከምን የተሠሩ እንደሆነ ተማሪዎች በጽሑፍ ዘርዝረው ጽፌው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡

በአከባቢዎ የልብስ ፋብሪካ ወይም የሽማኔ ቤት ካለ ፕሮግራም ይዘው በማስጎብኘት ልብሶቹ እንደተሠሩ የተመለከቱትን በጽሑፍ እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው፡፡

ቀጥለው መልመጃውን ያሰሯቸው፡፡ መልመጃውን ሲሰሩ ማስታወሻ ላይ ከተጻፈው በተጨማሪ ወላጆቻቸውን ጠይቀው ከቆዳ ፣ከጥጥ፣ ከሀር፣ ክር፣ ወዘተ የሚሠሩ በማለት ለይተው ጽፌው እንዲያመጡ ያድርጓቸው፡፡

**ሰዋስው**

## ትምህርት አሥራ አንድ

### በተውላጣ ስሞች አረፍተ ነገር መመስረት

መምህር/ት፡- ተማሪዎቹ ስለ ሰዋስው በቂ ግንዛቤ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ ስም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡ **ተውላጣ ስሞች የሚባሉት፡-** እኔ፣ አንቺ፣ እሷ ወዘተ ስለመሆናቸው ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም **በተውላጣ ስሞቹ** አጫጭር አረፍተ ነገሮችን እንዲመሠርቱ ያድርጓቸው፡፡

**መርጃ መሣርያ**

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ መሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ሥዕሎች፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሣርያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ግምገማ**

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት እንዲጽፉ በማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፤

**በአጠቃላይ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ ፡-**

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽ ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ ሁለት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥና የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ በአዳምጦ መናገር ስር የቀረቡት ምስሎችን፣ ስሞችንና የቀለሞችን አይነት በቁጥራቸው ልክ በትክክል እንዲጽፉ በማድረግ ማሰራት ይቻላል፡፡

**ሀ. አዳምጦ መናገር**

## ትምህርት ሶስት

**መልመጃ አንድ፡-**

1. ከቆዳ
2. ከጥጥ
3. ከክር
4. ከጥጥ
5. ከጥጥ

## ትምህርት አራት

**መልመጃ አንድ**

1. ከቆዳ

2. የሐመር ሴቶች ከላይ ደረታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት የቆዳ ጥብቆ ነው፡፡

3.የሐመር ሴቶች በዕድሜ ከፍ ሲሉ ከፊት ለፊታቸው የሚለብሱት አልባሳት ቶቆ የሚባል ሲሆን ፋላንቲ የሚባለው ባህላዊ አልባሳት ደግሞ ከቆዳ የሚዘጋጅ ባለጥንድ ጉርድ ቀሚስ ነው፡፡

4.የሐመር ሴቶች ከማግባታቸው በፊት የሚለብሱት ባህላዊ አልባሳት ቶቆ እና ፋላንቲ ይባላል፡፡

5.ከወገብ በታች ከፊት ለፊት ኢኮርባ ከኋላ ደግሞ ቡዱኮርባ የሚባለውን ባህላዊ አልባሳትን ይለብሳሉ፡፡

**ምንባብ**

## ትምህርት ስምንት

**መልመጃ አንድ፡-**

1.አንበሳ

2. የአራዊት ሁሉ አለቃ ቢባልም አውራ ዶሮን በመፍራቱ፡፡ ጅብን፣ ዝሆንን እና ጎሽን ሳይፈራ እዚህ ግባ ለማይባል ትንሽዬ አውራ ዶሮን በመፍራቱ፡፡ …

3.ዝሆንን

4.ዝሆን

5.ግዙፍ የሆነው ዝሆን ትንኝን በመፍራቱ እና ጆሮው ውስጥ ከገባች ስለምትገድለው፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት

**መጻፍ**

## ትምህርት አስር

**መልመጃ አንድ፡-**

1.የሀበሻ ቀሚስ፣ ጋቢ ፣ብሉኮ፣ ሱሪ፣ ሹራብ ወዘተ ናቸው።

2.ጃኬት፣ ዘመናዊ የሌዘር ጉርድ፣የሌዘር ታይት፣ ጫማ እና ቦርሳዎች ወዘተ ናቸው።

3.ብርድ ልብስ፣ እስክርብ፣ ሹራብ ወዘተ ናቸው።

**ሰዋስው**

**መልመጃ አንድ**

1.አንተ ትምህርት ቤት ሂድ!

2.አንቺ ጎበዝ ተማሪ ነሽ።

3.እሱ ማንበብ ይወዳል።

4.እሷ ትምህርት ቤት ሄደች።

5.እናንተ የቤት ስራችሁን ሰራችሁ?

# ምዕራፍ ሦስት

# የቤት ውስጥ መገልገያዎች

(የክፍለ ጊዜ ብዛት 10)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- በሥዕላዊ መግለጫዎች ተደግፈው የቀረቡትን የቤት ውስጥ መገልገያዎች ስማቸውን አዳምጠው ይናገራሉ፡፡
- ከሸክላና ከብረት የሚሰሩ የቤት ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ስያሜ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ይመሠርታሉ፡፡
- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ስም ይፅፋሉ፡፡
- የእውነት ሐሰት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- በተውላጣ ስሞች አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

## አዳምጦ መናገር

### አንደኛ ሳምንት ፡- ትምህርት አንድ

### የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ስያሜዎችን አዳምጦ መናገር

በዚህ ርዕስ ስር መምህር/ት ስለቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ምን ምን እንደሚያውቁ ተማሪዎቹን በቃል በመጠየቅ መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

ተማሪዎቹ እንደየ አካባቢያቸውና እንደየቤታቸው የሚጠቀሟቸውን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ስም እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ መልስ ሲሰጡ ባህላዊውንና ዘመናዊውን ለይተው ይናገሩ፡፡

መምህር/ት የተማሪ መፅሃፍ ይዘው በመቅረብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ከመጽሐፉ ያሳዩዋቸው፡፡

የሚከተሉትን ሥዕሉን የሚወክሉ ስሞች ይጻፉላቸው፡፡

የዕቃ መደርደሪያ፣ብረት፣ ድስት፣ ጀበና፣

ሲኒ፣ ቢላዋ፣ መክተፊያ፣

ማንኪያ፣ ሹካ፣ ማማሰያ፣

ወንፊት፣ ሸክላ፣ ድስት፣ ባልዲ፣

ማንደጃ፣ ምድጃ እና ማሰሮ

በመቀጠል መልመጃውን ያሰሯቸው፡፡

መልመጃዎቹ የንግግር ችሎታቸውን መመዘኛ ስለሆኑ ሁሉም ተማሪ በየተራ እየተናገሩ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

መልመጃ ሁለትም የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች ስለሆኑ መልሱን በቃል እንዲመልሱ ይጠይቋቸው፡፡

## ትምህርት ሁለት

### የቤት ቁሳቁሶችን ጥቅም መናገር

መምህር/ት፡- የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች የተለያዩ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ አንድ ተግባር ለመፈፀም የተለያዩ ዕቃዎችን መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- እንጀራ ለመጋገር፤ ምጣድ፣ አክንባሎ፣ ማሰሻ፣ ማዞሪያ፣ መሳቢያ፣ ጎመንዘር፣ ባልዲ፣ ላስቲክ፣ መሶብ ወዘተ ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህን መሰል ጥያቄዎች በማዘጋጀት ተማሪዎች እንዲናገሩ በማድረግ የንግግር ችሎታቸውን ያዳብሩ፡፡

በመቀጠል የሚከተሉትን የቤት ቁሳቁሶች ስም የያዙ ቃላት እያነበቡላቸው በእያንዳንዱ ቃል አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

**ቃላት፡- ጉልቻ**

**ሰፌድ**

**አገልግል**

**አግዳሚ ወንበር**

**ገንቦ አልጋ**

**የጥጥ ፍራሽ**

**ብርኩማ**

## ትምህርት ሦስት፡- ማዳመጥ

መምህር/ት፡- የተማሪዎችን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ችሎታቸው እንዲዳብር ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያዳመጡትን፤ የተለያየ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች በክፍል ውስጥ በንግግር አንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ያበረታቷቸው፡፡

**ማንበብ**

## ሁለተኛ ሳምንት ፡-ትምህርት አራት

**የቤት ቁሳቁሶችን ስም ማንበብ**

መምህር/ት በቅድሚያ በአካባቢያቸው ወይም በቤታቸው የሚገኙ (የሚያውቁ) የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን እንዲጠሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል በተማሪ መፅሐፍ የተዘረዘሩትን የቤት ቁሳቁሶች ስም ያስነብቧቸው፡፡

እያንዳንዱ ዕቃ ለምን አገልግሎት እንደሚውል ጠይቀው ተማሪዎቹ መልሶቻቸውን ካቀረቡ በኋላ መልመጃውን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የእያንዳንዱን ጥያቄ መልስ ደብተራቸው ላይ ከሰሩ በኋላ በንባብ እንዲያሰሙ ያበረታቷቸው፡፡

**ማስታወሻ፡-**

ተማሪዎች የፅህፈት ክሂልን ከታችኛው ክፍል ጀምሮ እንዲለማመዱ የማድረግ ዋና ዓላማዎች፡-

•የቋንቋውን ፊደላት ለይተውና የጽህፈት ሥርዓትን አውቀው

በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማስቻል፤

• የሚፈለጉና የማይፈለጉ መረጃዎችን መርጦ ለመጠቀም፤

• የቋንቋውን ስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ለመረዳት፤

•ጽሑፉን አንባቢው በሚረዳው መልክ ለማደራጀትና መልዕክትን በተገቢው ለማስተላለፍ በሚገባ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

ጽሕፈትን በሁለት የማስተማሪያ ዘዴ ማስተማር ይቻላል፡፡ እነርሱም፡- ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር ናቸው፡፡

ሂደት ተኮር የሚባለው የማስተማሪያ ዘዴ መጻፍን ለማስተማር ሥራ ላይ በሚውሉ ሞዴሎች አማካይነት ጽሕፈትን ማስተማር ሲሆን ሂደቱም ከቀላሉ በመጀመር ወደ ከባዱ የጽሕፈት ሥራ የሚዘልቅ ነው፡፡ ይህዓይነቱ የማስተማሪያ ስልት ለተማሪዎች የሚመች ስለሆነ ከፊደል ቀረጻ ጀምሮ በሂደት ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

(ከቀድሞ የ4ኛ ክፍል አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ

የመምህሩ መምሪያ ላይ የተወሰደ)

መምህር/ት ከላይ ከቀረበው ጽሑፍ እንደምንረዳው የጽሕፈት ሥራ ከፊደል ቀረጻ ይጀምራል፡፡ በሂደትም ቃላት፣ ሀረጎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ አንቀፅ እየተባለ ያድጋል፡፡ ተማሪዎችም ይህን ሂደት በቅደምተከተል ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**መፃፍ**

## ትምህርት አምስት

### የቤት ውስጥ መገልገያ መሳሪያዎችን ስም መፃፍ

መምህር/ት በዚህ ክፍል የቀረበው የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ስም ዝርዝር መጻፍነው፡፡ በተማሪ መፅሐፍ ከቀረበው በተጨማሪ ሌሎች መገልገያዎችንም በማዘጋጀት በቃል እንዲጽፉ ቢያደርጓቸው አዳምጦ የመጻፍ ልምድ ያዳብርላቸዋል፡፡

በመቀጠል መልመጃውን ያሰሯቸው፡፡ መልመጃውን ሲሰሩ ለአንድ ምግብ ዝግጅት የሚያስፈልጉትን ሙሉ ዕቃዎች በዝርዝር እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

እንደዚሁም በሥዕል የቀረቡትን ሥዕሉን ተመልክተው የመገልገያ ዕቃውን ስም መጻፍ መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

## ትምህርት ስድስት

### አረፍተ ነገሮችን ከመደብ አንጻር መጻፍ

መምህር/ት ይህን ክፍል ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት የስምና የተውላጠ ስምን ልዩነት ያስረዷቸው፡፡ ተውላጠ ስሞች የምንላቸው በስም ፈንታ የሚገቡ መደብን፣ ፆታን፣ ቁጥርን፣ ሊያመለክቱ

የሚችሉ ስሞች ናቸው፡፡ በነዚህ ስሞች መነሻ በእያንዳንዱ አረፍት ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፡

***መርጃ መሣርያ***

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ሥዕሎች፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሣርያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

***ግምገማ***

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩበጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት እንዲጽፉበማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩማበረታቻዎችን መስጠት፤

**በአጠቃላይ**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ

- ➢ በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

▸ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነትምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽን ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ ሶስት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥና የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ በአዳምጦ መናገር ስር የቀረቡት ምስሎችን፣ ስሞችንና የቀለሞችን አይነት በቁጥራቸው ልክ በትክክል እንዲጽፉ በማድረግ ማሰራት ይቻላል፡፡

**ማንበብ**

**ትምህርት አራት**

**መልመጃ አንድ፡-**

1. በመክተፊያ
2. የድንጋይ ወፍጮ
3. ሰፌድ
4. ማንኪያ
5. መሶብ
6. በርጩማ

**መጻፍ**

## ትምህርት ስድስት

እኔ ማንበብ እችላለው፡፡

1. አንተ ማንበብ ትችላልህ?
2. አንቺ መጻፍ ትችያለሽ?
3. እሱ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡
4. እኛ ማንበብ እንችላለን፡፡
5. እናንተ መጻፍ ትችላላችሁ?

# ምዕራፍ አራት

# የንጽህና አጠባበቅ

**(ክፍለ ጊዜ ብዛት 12)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ትምህርት በሚገባ ከተማሩ በኋላ፡-**

- የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስያሜ አዳምጠው ይናገራሉ፡፡
- ስለግልና አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ሲነገር ወይም ሲነበብ አዳምጠው ይናገራሉ፡፡
- ስለኮሮና ቫይረስ ምንነት አንብባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ስለግልና አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ጠቀሜታ ይናገራሉ፡፡
- ስለግልና አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ መንገዶችን ይናገራሉ እንዲሁም ይጽፋሉ፡፡
- ከምንባብ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- ከንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን፣ሐረጋትን ዐ.ነገሮችን ያነባሉ እንዲሁም ይጽፋሉ፡፡
- ከንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን ተጠቅመው ቀለል ያለ አረፍተ ነገር ይመሠርታሉ፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት አንድ

### አዳምጦ መናገር

**የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስያሜ አዳምጦ መናገር**

መምህር/ት፡- እባክዎን የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለማወቅ የግል ንጽህና ምን ማለት እንደሆነና የግል ንጽህናን ለመጠበቅ ምን ምን ነገሮች እንደሚያስፈልጉ ያደመጡትን እንዲናገሩ ያድርጓቸው ፡፡

መምህር/ት፡- እባክዎን ተማሪ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስዕል እያሳዩ ሰሌዳ ላይ ከፃፏቸው ቃላት ስያሜያቸውን እየወሰዱ በቁጥር ትይዩ በጥቁር ሰሌዳ በመጻፍ ያንብቡላቸው፡፡

ያዳመጡትንም የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን በትክክል መጥራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡

መልመጃውን ሲያሰሩ የእያንዳንዱን የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን በቃል እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው፡፡

- የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ቃል ያንብቡላቸው ፡፡
- በስዕል ተደግፎ የቀረበውን የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስያሜ እንዲነግሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስያሜ ቃል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፏቸው፡፡
- በተማሪው መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የግል ንጽህና መጠበቂያ ስዕላዊ መግለጫውን እያሳዩ የእያንዳንዱን መጠሪያ ቃል ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት ሁለት

### የአከባቢ ንጽህና አጠባበቅ ጥቅም

መምህር/ት ተማሪዎቹ የግል ንጽህና ለመጠበቅ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ለይተው ማወቃቸውን ለጥያቄዎቹ ከሚሰጡት መልስ መነሻነት ይከታተሉ ።

በመቀጠልም መልመጃውን ያሰሩ፡፡ መልመጃውን ሲያሰሩ የግልና የአከባቢ ንጽህና ባለመጠበቅ ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸው፡፡

አከባቢያቸውን ለማጽዳት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት ሶስት

### የግል ና የአካባቢ ንጽህና መጓደል የሚያመጣው ጉዳት

መምህር/ት በተማሪ መጽሐፍ ላይ ለቀረበው መልመጃ የሚከተለው ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን ረጋ ብለው ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ በመቀጠልም ለጥያቄው ተገቢውን መልስ በቃል እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

# የግልና የአካባቢ ንጽህና

የግል ንጽህና ማለት ሰው ለእራሱ ሰውነት እና ለሚለብሰው ልብስ የሚያደርገው ጥንቃቄ ማለት ነው። የአካባቢ ንጽህና ማለት ደግሞ አካባቢያችንን ከተለያዩ ተረፈ ምርቶች ምክንያት የተነሳ እንዳይቆሸሽ ጽዱና ንጹህ እንዲሆን ማድረግ ነው።

ከግል ንጽህና ጋር ተያይዞ የምናከናውናቸው በርካታ ተግባራቶች አሉ። እነሱም እጅን፣ እግርንና ፊትን መታጠብ፣ የእጅና እግርን ጥፍር መቁረጥ፣ገላን መታጠብ፣ ጥርስን በሚገባ መፋቅ እንዲሁም ልብስን ማጠብ፣መተኮስና የመሳሰሉት ናቸው። የአካባቢያችንን ንጽህና ለመጠበቅ የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎችም መጥረጊያ፣ መቆፈሪያ፣ ቅርጫት እና የመሳሰሉት ናቸው። ከአካባቢ ንጽህና ጋር ተያይዞ የምናከናውናቸው ተግባራት አሉ። እነሱም አካባቢያችንን ማጽዳት፣ ተረፈ ምርቶችን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድ፣ የቤት ውስጥ ፍሳሾችን በአግባቡ ማስወገድ፣ በግቢያችንና በአካባቢያችን ውሃ ያቆረ ቦታ ካሉ ማስወገድ እና የመሳ የግልና የአካባቢ ንጽህናችንን ከምንጠብቅባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ ከንጽህና ጉድለት ምክንያትየተነሳ የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከል፣ የቆዳ በሽታ፣ ትራኮማ፣ የወስፋት፣ የወባ በሽታና የመሳሰሉት ናቸው። ስለዚህም ከንጽህና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች አብዛኞቹ በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፉ ናቸው። ስለዚህም እኛ ንጽህናችንን ካልጠበቅንና በዚህ ምክንያት የተነሳ በተለያዩ የግል ንጽህና ጉድለት በሚመጡ በሽታዎች ከተጠቃን በሽታውን በቀላሉ ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ስለምንችል የራሳችንንና የአካባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ የግድ ይሆናል ማለት ነው።

## ትምህርት አራት

### አንብቦ መረዳት

#### ምንባብ

መምህር/ት በዚህ ክፍል ወቅታዊ ጉዳይን የያዘ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት ኮሮና ቫይረስ ምን እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡ በሽታ (ወረርሽኝ) መሆኑን ከተገነዘቡ መከላከያ መንገዶቹን እንዲያስረዱ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ምንባቡን ረጋ ብለው ሁለት ጊዜ እንዲያነቡት ያድርጓቸው፡፡

ዋናው ጉዳይ ተማሪዎቹ በሽታው ሁሉንም ሰው መግደል የሚችል መሆኑን እንዲያውቁና የበኩላቸውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው፡፡ ስለዚህ መልመጃዎቹን ሲያሰሩ በቅድሚያ ስላነበቡት ጉዳይ ጠቅላላ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ይጠይቋቸው፡፡ ስለበሽታው ትክክለኛ ግንዛቤ መያዛቸውን ያረጋግጡ፡፡

መምህር/ት ዝርዝር መረጃውን በቅደም ተከተል ስለ ማስቀመጣቸው ያረጋግጡ፡፡

በጥንድ ተወያይተው የግልና የጋራ  ንጽህና መጠበቂያ ሂደትን በጋራ ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ግንዛቤ መፍጠር ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድና ሁለትን ያሰሯቸው፡፡

## ማንበብ

## ትምህርት አምስት

### የግል ንጽህና አጠባበቅ

መምህር/ት በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የግል ንጽህና የተሰኘውን ምንባብ ተማሪዎችን በማስነሳት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ምንባቡን ቀድሞ የቀረበውን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር/ት ሶስቱንም የንባብ ተግባራት ልምምድ ጥያቄዎችን በተገቢው መልኩ ስለመስራታቸው ያረጋግጡ፣ ይከታተሉ፡፡

የምንባቡን መልዕክት በትክክል ስለመረዳታቸው ያረጋግጡ፡፡

## ትምህርት ስድስት

### ቃላትን ፣ ሐረጋትንና አረፍተ ነገሮችን ማንበብ

መምህር/ት በዚህ መዕራፍ ውስጥ የቀረበው ትምህርት ስለ ግልና አካባቢ ንጽህና በመሆኑ ተማሪዎች የአካባቢና የግል ንጽህናን የሚጠቁሙ ቃላትን፣ ሐረጋትን ድምጽ እያሰሙ እንዲያነቡ ለማድረግ በቻርት ወይም በፍላሽ ካርድ ጽሑፎችን አዘጋጅተው ያቅርቡ፡፡ ከዚያም ክፍል ውስጥ ድምጻቸውን በማሰማት አንዲያነቡ ይድርጓቸው፡፡

መምህር/ት በዚህ ክፍል የግልና የአከባቢ ንጽህናን መሠረት ያደረገ ቃላትና ሀረጋት ያልቀረበ ካለ አካቶ ማቅረብ ይቻላል፡፡

መምህር/ት ቃላቱንና ሀረጋቱን በትክክል ማንበብ ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡

ቃላቱንና ሀረጋቱን ድምጽ በማሰማት በትክክል ስለማንበባቸው ይከታተሉ፡፡

መምህር/ት በዚህ ክፍል ውስጥ የግል ንጽህናን መሠረት ያደረጉዐ.ነገሮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን አረፍተ ነገሮች በትክክል ድምጽ አሰምቶ ለማንበብና ለመከታተል ያመች ዘንድ በቻርት ወይም በፍላሽ ካርድ ጽሑፎችንበማዘጋጀት ያቅርቡ፡፡ በመቀጠልም በክፍል ውስጥ ካርዱን በመለዋወጥ ተራ በተራ ድምጽ እያሰሙ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር/ት ሌሎች የግል ንጽህናን መሠረት ያደረጉ አረፍተ ነገሮች ካሉ መጨመር ይቻላል፡፡

መምህር/ት ተማሪዎቹ አረፍተ ነገሮቹን በትክክል ማንበብ ስለመቻላቸው ይከታተሉ፡፡ አንብበው ስለመጨረሳቸውም ያረጋግጡ፡፡

**መፃፍ**

## ሶስተኛ ሳምንት፡-ትምህርት ሰባት

### አዳምጦ መፃፍ

መምህር/ት፡- በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ተግባር ተማሪዎች ከክፍል ወጣ ብለው መረጃ መሠብሠብ የሚያስችሏቸው ልምምድ በመሆኑ በጥያቄ ዙርያ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

መምህር/ት፡- ተማሪዎች አካባቢያቸው ወዳለው ጤና ጣቢያ በመሄድ ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅና የግል ንጽህናችንን ባለመጠበቃችን ሊከሰት ስለሚችሉ የጤና ዕክሎች መረጃ እንዲሰበስቡ ያድርጉ በተጨማሪም ስለ አካባቢ ንጽህና መጠበቂያ መንገዶችና አካባቢያችን ባይጸዳ ከጤና ችግር ጋር ተያያዥ ስለሆኑና ሊከሰቱ ስለሚችሉ ጉዳዮች መረጃ በማጠናከር እንዲጽፉና አዳምጦ የመጻፍ ልምዳቸውንም እንዲያዳብሩ ያግዟቸው፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች በትክክል መጻፍ ስለመቻላቸው ይከታተሉ፡፡ መረጃውን በጥሩ ሁኔታ አጠናክረው ስለመጻፋቸውም ያረጋግጡ፡፡

መምህር/ት፡- በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረበው ሌላው ተግባር ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

ስለሆነም የግል ንጽህና መጠበቅ መሣሪያን የግል ንጽህናችንን መጠበቅ በመቻላችንና ባለመቻላችን ሊከሡቱ ስለሚችሉ ችግሮች መሠረት ያደረገ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ የቀረበው መልመጃ የተሟላ መልዕክት እንዲይዝ የተለያዩ ቃላትና ሀረጋት ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ቃላትና ሀረጋት በተገቢው ቦታ ላይ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡

መምህር/ት እባኮትን የቀረበው ተግባር የተሟላ ሀሳብ እንዲኖረው ቃላትን/ሀረጋትን በትክክልና በተገቢው ሁኔታ ተማሪዎች አሟልተው ስለመጻፋቸው ይከታተሉ፡፡ በትክክል በተገቢው ቦታላይ ስለመጻፋቸው ያረጋግጡ፡፡

መምህር/ት ስለ ግልና አከባቢ ንጽህና መሠረት ያደረገ በክፍት ቦታ ላይ ቃላትን /ሀረጋትን ማሟላት የሚያስችል ሌሎች ተግባራትን አዘጋጅቶ ማካተት ይቻላል፡፡

መምህር/ት ይህን ልምምድ በጥንድም ሆነ በግልም እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ተማሪ በትክክል መጻፍ ስለመቻላቸው ክትትሉና ድጋፉ ይጠናከር፡፡

## ሶስተኛ ሳምንት፡- ትምህርት ስምንት

### በንጽህና ላይ የሚያተኩሩ ተራ ዐ.ነገሮችን መጻፍ

መምህር/ት ተማሪዎች ንጽህናን መሠረት ያደረጉ ቃላትን ተጠቅመው በርካታ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሠርቱ ያድርጓቸው፡፡ ዐ.ነገሩንም በትክክል መጻፍ ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡ ሁሉንም የንጽህና አይነቶች በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በትክክል መካተት ስለመቻሉ ይከታተሉ ፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች የጻፉትን አረፍተ ነገር በክፍል ውስጥ በንባብ እንዲያሰሙ ያድርጉ፡፡

ማሳሰቢያ ( ስለ አቀራረብ)

- ✓ ተማሪዎች በመማር ሂደት ውስጥ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ መሻሻልና መለወጥ እንዲችሉና ሀሳብ እርስ በርስ መለዋወጥ እንዲችሉ በጥንድ እና በቡድን ማደራጀት፡፡
- ✓ ተማሪዎች ካነበቡት፣ ካዳመጡት ውስጥ ስለ ግል ንጽህና አስመልክቶ ተተኳሪውን ነጥብ (ይዘት ) እንዲናገሩ ማነቃቃት ወይም ማበረታታት፡፡
- ✓ ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ ሆነው ስለግል ንጽህና እና ስለአከባቢ ንጽህና እንዲወያዩ በማድረግ የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ማገዝ፤
- ✓ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ስለ ግል እና አከባቢንጽህናን መሠረት ያደረገ አጫጭር ጽሑፎችን እንዲጽፉ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ በዚህም የማዳመጥና መናገር ክሂላቸው እንዲዳብር ማገዝ፡፡
- ✓ አስፈላጊ የሆኑመርጃ መሣርያዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተ ነገር እንዲያውቁ ማድረግ እንዲሁም በቋንቋውየማዳመጥ፣ የመናገር ፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂላቸውን ማለማመድ፤ ዋናው የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ መተግበሪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎች በጥንድ፣ በቡድንና በግል በመሆን መልመጃዎችን እንዲሠሩ ማድረግና ማበረታታት ያስፈልጋል ፡፡

### መርጃ መሣሪያ

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በመርጃ መሣርያነት የሚያገለግሉ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም ከተመረጠው የትምህርት ይዘት ጋር ተጣጥሞ ሊሄድ የሚችለው የግል ንጽህና መጠበቂያ መሳሪያዎችን የያዙ ስዕሎች እንዲሁም በጋራ ሆነው አካባቢያቸውን ሲያፀዱ የሚያሳዩ ስዕሎች ናቸው፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ተስማሚ የሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን ማገዝና ክፍለ ጊዜውን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

### ግምገማ

በዚህ ምዕራፍ አራት ላይ የቀረቡትን ተግባራት በክፍልና ከክፍል ውጭ በግልና በጥንድ እንዲተገብሩ ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት ይገባል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የአካባቢን ገጽታ በሚመለከት የቀረቡትን የተለያዩ ስዕሎች  በመመልከት ተማሪዎች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡  ተማሪዎች የሰጡትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ በአጠቃላይ በትምህርቱ አቀራረብ እንደተገለጸው የሚከተሉትን  የመገምገሚያ ስልቶች በመጠቀም የተግባር ግምገማ ማድረግ ይቻላል፡፡ የቃልጥያቄ፣ የጥንድ ስራ እና የክፍል ስራ ናቸው፡፡ በተጨማሪም፡ -

- ✓ ተማሪዎች ከቀረበላቸው መልመጃ /ተግባራት / ውስጥ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

**በአጠቃላይ ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ተማሪዎች በምዕራፉ የቀረቡትንየትምህርት ይዘት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በቋንቋቸውናበሚማሩበት ቋንቋ መካከል ሚፈጠሩ የድምጽ ንበት ስህተቶችን በአዎንታ ጎን በመመልከት እና ስህተቱ ተፈጥሯዊ መሆኑን በመረዳት ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ አራት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኞዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር እና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹም ስዕሎችንና ምንባብን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ግን ቁርጥ ያለ ምላሽን የሚሹ ናቸው፡፡

አዳምጦ መረዳት

## ትምህርት ሶስት

## የግልና የአካባቢ ንጽህና መጓደል የሚያመጣው ጉዳት

መልመጃ፡-

1. የግል ንጽህና ማለት ሰው ለእራሱ ሰውነት እና ለሚለብሰው ልብስ የሚያደርገው ጥንቃቄ ማለት ነው፡፡
2. የአካባቢያችንን ንጽህና ለመጠበቅ ከሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ውስጥ፡- መጥረጊያ፣ መቆፈሪያ፣ ቅርጫት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

   ከአካባቢ ንጽህና ጋር ተያይዞ የምናከናውናቸው በርካታ ተግባራት ያሉ ሲሆን እነሱም፡- አካባቢያችንን ማጽዳት፣ ተረፈ ምርቶችን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድ፣ የቤት ውስጥ ፍሳሾችን በአግባቡ ማስወገድ፣ በግቢያችንና በአካባቢያችን ውሃ ያቆሩ ቦታዎች ካሉ ማስወገድ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. የግልና የአካባቢ ንጽህናችንን በሚገባ መጠበቅ መቻል አለብን፡፡
4. ከንጽህና ጉድለት ምክንያት የተነሳ ለሚከሰቱ በሽታዎች ያጋልጠናል፡፡ ከነዚህም መካከል የቆዳ በሽታ፣ ትራኮማ፣ ወስፋት፣ የወባ በሽታና ለመሳሰሉት በሽታዎች ይዳርጋል፡፡ ስለዚህም ከንጽህና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች አብዛኞቹ በቀላሉ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፉ በመሆናቸው የአንድ ግለሰብ እና የአካባቢ ጽዳት ለሌው ግለሰብ ጤንነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

# ትምህርት አራት

## የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ ሂደት በቅደም ተከተል አዳምጦ መናገር

**መልመጃ አንድ፡-**

1.ሀ

2.ሀ

3.ለ

4.ሀ

5.ሀ

**መልመጃ ሁለት፡-**

1.እውነት

2.እውነት

3.ሐሰት

4.እውነት

5.ሐሰት

ማንበብ

## ትምህርት አምስት፡ -

### የግል ንፅህና አጠባበቅ

**መልመጃ፡-**

1. የግል ንፅህና መጠበቅ የፊት፣ የጥርስ፣ የፀጉር፣ የአካላችንንና የልብሳችንን ንፅህና መጠበቅ ማለት ነው፡፡
2. በተለያዩ የፅዳት ጉድለቶች ምክንያት የተነሳ የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከል፣ ጤናማ የሆነ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲኖረን፣ ከሰዎች ጋር ጤናማ የሆነ አብሮነትን ለመፍጠር እና ጤናችን የተስተካከለና በጥሩ አቋም ላይ እንዲገኝ ነው፡፡
3. ፊታችንና እጃችንን በሳሙና በመታጠብ፣ ቁርስ ከመመገባችን በፊት እና ከእራት በኋላ ጥርሳችንን በጥርስ ሳሙና በማፅዳት፣ የእጃችንን ጥፍር ካደገ የተለያዩ ጀርሞችን ሊይዝ ስለሚችል ይህን በመቁረጥ፣ ፀጉራችን በፈንገስ እንዳይጠቃ በየግዜው በመታጠብ፣ ገላችን አላስፈላጊ የላብ ጠረን  እንዳያስተናግድ በየቀኑ በመታጠብ ንህፅናችንን መጠበቅ እንችላለን፡፡
4. ጥፍራችን የተለያዩ ጀርሞችን ሊይዝ ስለሚችል ነው፡፡

**መፃፍ**

**ትምህርት ሰባት፡ -**

**አዳምጦ መፃፍ**

**መልመጃ ሁለት፡-**

1. የጥርስ ሳሙና
2. ከፈንገስ
3. የላብ ጠረን
4. ለትራኮማ
5. ለቆዳ በሽታ

# ምዕራፍ አምስት

## መጓጓዣ

(የክፍለ ጊዜ ብዛት 10)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ያብራራሉ፡፡
- የመጓጓዣ ስዕሉን በማየት ከስያሜያቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ስለ ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አገልግሎትየቀረቡትን ማስታወሻዎች ያነባሉ፡፡
- ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- የመጓጓዣን አገልግሎት አስመልክቶ በጭውውት ሀሳብን ይለዋወጣሉ፡፡
- የነጠላና ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጣ ስሞችን ይለያሉ፡፡

### አዳምጦ መናገር

### አንደኛ ሳምንት ፡- ትምህርት አንድ

### የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን መናገር

መምህር/ት ቀጥታ ወደ ትምህርቱ ይዘት ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉትን የመጓጓዣ አይነቶችን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች አካባቢያቸውን በተወሰነ መልኩ እንዲያስቡና በተነቃቃ መንፈስ ወደ ዋናው ትምህርት ይዘት

እንዲገቡ ያስችላል፡፡ በመቀጠልም የቀረበውን ማስታወሻ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎቹ ምን ያህል እንደተረዱ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችንም ይጠይቋቸው፡፡

መምህር/ት የቀረቡትን ስዕሎች ተማሪዎቹ በአጽንኦት ተመልክተው የመጓጓዣ ስያሜዎችን እንዲናገሩ ያድርጉ፤ እንዲሁም በስዕል መልክ የቀረቡት ዘመናዊ ማጓጓዣዎች የሚጓዙበትን መንገድ እንዲናገሩ ይርዷቸው፡፡

መምህር/ት በዚሁ ትምህርት ክፍል ውስጥ የቀረበውን የመልመጃ ሁለት ከ ሀ እስከ ሠ ድረስ ያለውን ጥያቄ ተማሪዎች ስዕሉ ላይ ተመስርተው ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

## ትምህርት ሁለት

### ምስሎቹን ተመልክቶ የመጓጓዣ አይነቶችን መግለጽ

መምህር/ት ተማሪዎች ወደ ክፍለ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት ለተወሰነ ደቂቃ ያህል አካባቢያቸውን እንዲያስቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም በመኖሪያቸው አካባቢ ባህላዊ የመጓጓዣ አይነቶች ካሉ ስያሜያቸውን እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች በተነቃቃ መንፈስ ወደ ዋናው የትምህርት ይዘት እንዲገቡ ያስችላቸዋል፡፡

መምህር/ት በዚሁ ክፍለ ትምህርት ወስጥ ያለውን መልመጃ አንድ ሲያሰሯቸው ተማሪዎቹ በቀረበው ስዕላዊ መግለጫ ላይ ተመርኩዘው

መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡ ምናልባት ተማሪዎቹ የማያውቋቸው ስዕሎች ካሉ ገለጻ በማድረግ ይርዷቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መልመጃ ሁለትንም ያሰሯቸው፡፡

## ትምህት ሶስት፡- መናገር

መምህር/ት በመጀመሪያ ስለጭውውት አስመልክቶ የቀረበውን ማስታወሻ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎች ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች በሁለት ሰዎች መካከል የቀረበውን የሀሳብ ልውውጥ መሰረት አድርገው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ሌላ ጭውውት እንዲከውኑ ያድርጉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ትምህርቱ የቀረበበትን ቋንቋ ተጠቅመው ሀሳባቸውን በሚገባ መግለጽና የሌሎች ሰዎችንም ሀሳብ በጥሩ ሁኔታ መረዳት እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች በዚሁ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ያለው መልመጃ ሁለት ከ1 እስከ 7 ያሉትን ጥያቄዎች ሲያሰሯቸው ስለጭውውት አስመልክቶ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት አድርገው መሆኑን ያስታውሷቸው፡፡

## ትምህርት አራት፡-

### ማንበብ

መምህር/ት በቀጥታ ወደ ትምህርቱ ይዘት ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎችን ከዘመናዊና ከባህላዊ መጓጓዣ የትኛው እንደሚሻል ይጠይቋቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች በተነቃቃ መንፈስ ወደ ዋናው የትምህርት ይዘት እንዲገቡ ያግዛቸዋል፡፡ በመቀጠልም ስለባህላዊና ዘመናዊ የማጓጓዣ የቀረበውን ማስታወሻ አንዴ በዝግታ ካነበቡላቸው በኋላ ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ይህም የተማሪዎች የንባብክሂል እንዲዳብር ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ሁሉም ተማሪዎች እንዲያነቡ እድል ይስጧቸው፡፡

### መፃፍ

## ትምህርት አምስት፡-

መምህር/ት በቀጥታ ወደ ትምህርቱ ይዘት ከመግባትዎ በፊት አካባቢያቸውን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች በተነቃቃ መንፈስ ወደ ትምህርቱ ይዘት እንዲገቡ ያስችላል፡፡

### ምንባብ

የትራፊክ ህግ የምንላቸው ቀይ መብራት ሲበራ መኪናዎች ሲቆሙ በዜብራ መንገድ መሻገር፣ ግራ እና ቀኝ ይዞ መሄድ፣ ለእግረኛ የተሰራ መተላለፊያ (ዜብራ) መንገድ ይዞ መሻገር ይገባል፡፡ ሌላው

ደግሞ የቆመ መኪና ላይ ተለጥፎ መሻገር ለተለያዩ አደጋዎች ስለሚያጋልጥ የመኪና መንገድ ስንሻገር ግራና ቀኝ አይተን መሻገር አለብን፡፡ በዜብራ መንገድ ስንሻገር ስልክ ይዞ እያወሩ አለመሄድ፤ ሙሉ ትኩረታችን የአስፋልቱን ግራና ቀኝ አይቶ በጥንቃቄ መሻገር ላይ ይሁን፡፡

- ❖ ይህ ምንባብ ከትራፊክ አደጋ ራሳችንን እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ይረዳናል፡፡

መምህር/ት፡- በመቀጠል ከላይ የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ካነበቡላቸው በኋላ መልመጃ አንድ ስር የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ በትክክል የሰሩትንም ተማሪዎች ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር/ት** በዚሁ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ከ ሀ እስከ ረ ድረስ የቀረቡትን ባህላዊና ዘመናዊ የማጓጓዣ ስያሜ ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ ስያሜውን ተጠቅመው አረፍተ ነገር የመሰረቱትን ተማሪዎችንም ያበረታቷቸው፡፡

መምህር/ት እባክዎ ወደ ትምህርቱ ይዘት ከመግባትዎ በፊት ስለውሃ ላይና ስለየብስ ማጓጓዣ አይነቶችና ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ ተነተርሰው ግልጽ የሆነ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠልም በዚሁ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የቀረበውን መልመጃ ሶስት ላይ በ”ሀ” ምድብ የቀረቡትን የመጓጓዣ ስያሜ በ “ለ” ምድብ ከቀረበው ምስል ጋ በትክክል እንድያዛምዱ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት

### ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ለይቶ መጻፍ

መምህር/ት በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶች የቀረቡ ሲሆን፤ ተማሪዎች እነዚህን ስያሜዎች በየምድባቸው በጽሁፍ እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው፡፡

### ትምህርት ሰባት፡- ሰዋስው

መምህር/ት ወደ ክፍለ ትምህርቱ ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎች ምዕራፍ አንድ ላይ ስለ ተውላጠ ስም እና ስም የተማሩትን በማስታወስ ምንነታቸውን እንዲገልጹ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ለመቃኘት ያስችላል፡፡ እርሶም ተጨማሪ ገለጻ ካስፈለገ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠልም በቀረበው ምሳሌ መሰረት መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መልመጃ ሁለት ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

### መርጃ መሣርያ

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም የተለያዩ ሥዕሎች፣ ግራፎችና ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ በርካታ ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ ስዕሎችን የያዘ ቻርት በማዘጋጀት ፤ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

ግምገማ

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን የትምህርት ይዘት ምንያህል ግንዛቤ እንዳላቸው በመገምገም፤ በመከታተል

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፤

**በአጠቃላይ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡
- **ማሳሰቢያ፡-**

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽ ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ መልሶች

በምዕራፍ አምስት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥና የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ በአዳምጦ መናገር ስር የቀረቡት ምስሎችን፣ ስሞችንአይነት በቁጥራቸው ልክ በትክክል እንዲጽፉ በማድረግ ማሰራት ይቻላል፡፡

### አዳምጦ መናገር

### ትምህርት አንድ፡-

**የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን መናገር**

**መልመጃ አንድ ፡- (ለ) ምድብ**

1. ባጃጅ = ባጃጅ በየብስ (በመሬት ላይ የሚሄድ ነው፡፡)
2. አውሮፕላን = አውሮፕላን በአየር ላይ የሚሄድ ነው፡፡
3. መርከብ = መርከብ በውሃ ላይ የሚሄድ ነው፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

| | |
|---|---|
| **ሀ** | እውነት |
| **ለ** | ሐሰት |
| **ሐ** | ሐሰት |
| **መ** | እውነት |
| **ሠ** | ሐሰት |

## ትምህርት ሁለት

### ምስሎቹን ተመልክቶ የመጓጓዣ አይነቶችን መግለጽ፡፡

**መልመጃሁለት**

1.ሐ

2.ለ

3.መ

4.ሐ

5.ለ

## ትምህት ሶስት፡-  መናገር

**መልመጃ ሁለት**

| | |
|---|---|
| 1 | ሐሰት |
| 2 | እውነት |
| 3 | ሐሰት |
| 4 | እውነት |
| 5 | ሐሰት |
| 6 | ሐሰት |
| 7 | እውነት |

**መፃፍ**

## ትምህርት አምስት

### መልመጃ ሁለት

ሀ. አህያ ጭነት ለመጫን ያገለግላል፡፡

ለ. አውሮፕላን ዘመናዊ መጓጓዣ ነው፡፡

ሐ. በቅሎ ባህላዊ መጓጓዣ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## ትምህርት ስድስት

### ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ለይቶ መጻፍ

### መልመጃ አንድ

| ተ.ቁ | ባህላዊ መጓጓዣ | ዘመናዊ መጓጓዣ |
|---|---|---|
| 1 | ፈረስ | አውሮፕላን |
| 2 | አህያ | ሂሊኮፍተር |
| 3 | በቅሎ | ሞተር ሳይክል |
| 4 | ታንኳ | አውቶብስ |
| 5 | ግመል | መርከብ |
| 6 | ፈረስ ጋሪ | ባቡር |
| 7 | ግመል | የቤት መኪና |

## ትምህርት ሰባት ፡ -

### ሰዋስው

### መልመጃ አንድ

| | |
|---|---|
| 1 | ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም ፡- አንተ (ለተባታይ ጾታ) |
| 2 | ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም፡- አንቺ (ለአንስታይ ጾታ) |
| 3 | ለብዙ ቁጠር አመልካች ተውላጠ ስም፡- እናንተ (ጾታ አይለይም) |
| 4 | ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም፡- እሱ (ለተባታይ ጾታ) |
| 5 | ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም ፡- እሷ (ለአንስታይ ጾታ) |
| 6 | ለብዙ ቁጠር አመልካች ተውላጠ ስም፡- እነርሱ (ጾታ አይለይም) |

# ምዕራፍ ስድስት

## የምግብ ዓይነትና አዘገጃጀት

(የክፍለ ጊዜ ብዛት10)

**የምዕራፉ አላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ትምህርት በሚገባ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በአካባቢያችሁ ስለሚገኙ የምግብ አይነቶችና አዘገጃጀት ይናገራሉ፡፡
- የምግብ ዝግጅት ሂደትን በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡
- በምግብ ጥቅሞች ዙሪያ የተዘጋጁ ምንባቦችን ያነባሉ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ የምግብ አይነቶችን በዝርዝር ይጽፋሉ፡፡
- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን አዘገጃጀት በጽሁፍ ያስረዳሉ፡፡
- የጎደሉ አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት አሟልታችሁ ይጽፋሉ፡፡

### አዳምጦ መናገር

### ሳምንት አንድ፡- ትምህርት አንድ

### የምግብ አይነቶች

መምህር/ት ይህንን ክፍል ለማስተማር በቅድሚያ የሚያውቋቸውን የምግብ አይነቶች እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያ ውስጥ ምን አይነት ምግብ እንደሚወዱና ለምን እንደሚወዱ ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድ ላይ በዝርዝር የቀረቡትን የምግብ አይነቶች

ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው። ይህም የተማሪዎችን የንባብ ክሂል በተወሰነ መልኩ እንዲዳብር ያስችላል።

በመቀጠል መልመጃ ሁለትን ያሰሯቸው። መልመጃውን ሲሰሩ ከተዘረዘረው የምግብ አይነት ውጪ በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን የተለያዩ የምግብ ዝርዝሮች እንዲናገሩ ያድርጓቸው። በአካባቢያቸው በበአላት ጊዜ የሚዘወትሩ ምግቦችንም ለክፍል ጓደኞቻቸው በመናገር ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያድርጓቸው። በአቅርቦት ስር ከቀረበው የምግብ ዝርዝር አዘውትረው የሚመገቡትን ወይም የሚያውቋቸውንና የማያውቋቸውን እንዲናገሩ ያነሷሷቸው።

## ትምህርት ሁለት

### የምግብ አይነቶችን በምድብ ከፋፍሎ መናገር

መምህር በቅድሚያ በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበውን ማስታወሻ አስመለክቶ ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠል የቀረበውን የተግባር ጥያቄ ከዚህ በታች በቀረበው ጽሁፍ መሰረት ያሰሯቸው። በየምድቡ ከተዘረዘሩት የምግብ አይነቶችን በመጥራት ገንቢ፣ በሽታ ተከላካይ ወይም ኃይል ሰጪ ምግብ እያሉ በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው።

**ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች**

ዳቦ

ቆጮ

ፓስታ

ስንዴ

ድንች

ጤፍ

አሣ

**ገንቢ ምግቦ**

እንቁለል

ባቄላ

አደንጓሬ

ወተት

የዶሮ ስጋ

የበግ ስጋ

አይብ

**በሽታ ተከላካይ**

ቃሪያቲማቲም

ሎሚ

ብርቱካን

አትክልትና ፍራፍሬ

## ትምህርት ሦስት

### ስለምግብ አዘገጃጀት መናገር

መምህር/ት ይህን ክፍል ሲያስተምሩ በአካባቢያቸው ለምግብነት የሚያገለግሉ ምግቦች ከምንና እንዴት እንደሚዘጋጅ እንዲናገሩ ያበረቷቷቸው፡፡ በመቀጠል በመልመጃው ስር የቀረቡ ምግቦች ከምን ከምን እንደተሳሩ በቃል እንዲያስረዱ ይገፏፏቸው፡፡

መምህር እባክዎ በዚህ ክፍል የቀረበውን የእርጎ አስፈላጊ ግብዓቶችና አዘገጃጀት ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡

**እርጎ**

**አስፈላጊ ግብዓቶች**

- 3 ሊትር ንፁህ የላም ወተት
- 1 የሾርባ ማንኪያ የሎሚ ጭማቂ
- እንጨት ወይራ ለማጠን
- ትንሽ ሚጥሚጣ

**አዘገጃጀት**፡-1. እርጎ ለማዘጋጀት አነስተኛ ገንቦ ወይንም ኪዳን ባለው ዕቃ ማዘጋጀትና በደንብ ማጠብ

2. የዘጋጀነውን ዕቃ ማድረቅና በወይራ በሚገባ ማጠን

3. ወተት በታጠነው ዕቃ ላይ አድርጎ የሎሚ ጭማቂውን በመክደን እርጎው እስኪረጋ ማቆየት

4.የተዘጋጀውን እርጎ በብርጭቆ ወይንም በሸክና አድርጎ ከሚጥሚጣ ጋር ማቅረብ ባርኮት የባህል ምግብና መጠጥ አዘገጃጀት፡፡

ሼፍ ካሱሰበቃና ሼፍ ዮናስ ተፈራ (2001 ዓ.ም፣ 155)

**ምንባብ**

## ትምህርት አራት

**አንብቦ መረዳት**

መምህር/ት ወደ ክፍለ ትምህርቱ ከመግባትዎ በፊት የቀረበውን የማነቃቂያ ጥያቄ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ይህም ከምንባቡ ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ምንባቡ ስለምን ሊያወሳ እንደሚችል ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋል፡፡ በመቀጠልም ማስታወሻውን በዝግታ የንባብ ስልት አንዴ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ተራ በተራ እያስነሱ ያስነብቧቸው፡፡ ይህም የተማሪዎችን አጥርቶ የማንበብ ክሂላቸው እንዲዳብር ዕገዛ ያደርግላቸዋል፡፡ አንብበው ሲያጠናቅቁ መልመጃውን በደብተራችሁ ላይ ሰርተው እንዲያሳዩ አድርጓቸው፡፡

## ትምህርት አምስት፡-

**የምግብ ክፍሎችን ማዛመድ**

መምህር/ት፡- በዚህ ክፍል ሁለት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ አንደኛው የምግብ ክፍሎችን ከምግብ አይነቶች ጋር ማዛመድ ሲሆን ሁለተኛው አረፍተ ነገርን ሙሉ አድጎ መጻፍ ነው፡፡ በሁለተኛው መልመጃ ስር የቀረቡትን ያልተማሉ ዓ.ነገሮች ሙሉ አድርገው ጽፈው ማሳየታቸውን ይከታተሉ፡፡

## ትምህርት ስድስት፡-

### አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መጻፍ

በዚህ ክፍል የተመጣጠነ ምግብን የሚያመለክት ሥዕላዊ መረጃ ቀርቦላቸዋል፡፡ መምህር/ት እባክዎ ተመሪዎቹ አረፍተ ነገር መመስረት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡ በተጨማሪ ጠቋሚ መረጃዎችን (ስዕላዊ መግለጫዎችን) ክፍል ውስጥ በማምጣት በደብተራቸው በመጻፍ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡

## ትምህርት ሰባት፡-

### ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ አንቀጽ መመስረት

መምህር/ት በዚህ ክፍል ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በአንድ ላይ በመጠቀም አንቀጽ የሚመሰረትበት ነው፡፡

በምሳሌው መሰረት ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ መመስረታቸውን ይከታተሉ፡፡

በመጨረሻም የአእምሮ ማበልጸጊያ ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡

***መርጃ መሣሪያ***

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በመርጃ መሣርያነት የሚያገለግሉ በርካታ ነገሮች ቢኖሩም ከተመረጠው የትምህርት ይዘት ጋር ተጣጥሞ ሊሄድ የሚችለው የግል ንጽህና መጠበቂያ መሳሪያዎችን የያዙ ስዕሎች እንዲሁም በጋራ ሆነው አካባቢያቸውን ሲያፀዱ የሚያሳዩ ስዕሎች ናቸው፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ተስማሚ የሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን ማገዝና ክፍለ ጊዜውን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

**ግምገማ**

- ተማሪዎች ከቀረበላቸው መልመጃ /ተግባራት / ውስጥ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

**በአጠቃላይ ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ተማሪዎች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በቋንቋቸውና በሚማሩበት ቋንቋ መካከል ሚፈጠሩ የድምጽ ንበት ስህተቶችን በአዎንታ ጎን በመመልከት እና ስህተቱ ተፈጥሯዊ መሆኑን በመረዳት ማብታታት ተገቢ ነው፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ ስድስት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኞዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር እና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ምስሎችንና ምንባብን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ግን ቁርጥ ያለ ምላሽን የሚሹ ናቸው፡፡

ምንባብ

## ትምህርት አራት

### አንብቦ መረዳት

**መልመጃ አንድ፡-**

1.በአራት

2.ሙዝ፣ ብርቱኳን፣ ሎሚ፣ ጎመን፣ ሰላጣ እና ቃሪያ ናቸው፡፡

3.ዳቦ፣ እንጀራ፣ ቂጣ፣ ገንፎ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ በቆሎ እና አተር ናቸው፡፡

4.እህል (ጥራጥሬ)

5.ከወተት ተዋጽኦ

## ትምህርት አምስት፡-

### የምግብ ክፍሎችን ማዛመድ

**መልመጃ አንድ**

1.ሀ

2.መ

3.ለ

4.ሐ

## ትምህርት ስድስት

### አጫጭር አረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ማድረግ

1.ስጋ በፕሮቲን የበለጸገ ነው፡፡

2.ማዕድን ከስጋ ይገኛል፡፡

3.ስብ ከእንስሳት ይገኛል፡፡

4.ጤፍ ካርቦሀይድሬትን ያስገኛል፡፡

5.ፍራፍሬ በቫይታሚን የበለጸገ ነው፡፡

## ትምህርት ሰባት

### አይብ ለማዘጋጀት የሚረዱ አስፈላጊ ግብአቶች፡-

- የተናጠ የላም ወተት
- ቅመማ ቅመም
- ሚጥሚጣ
- የተነጠረ ለጋ ቅቤ
- ጨው

**አዘገጃጀት፡-**

የተናጠው የላም ወተት አነስ ባለ እሳት ላይ በድስት ይጣዳል፡፡ ከተወሰነ ቆይታ በኋላ አይቡ እና አጓቱ ሲጠል ከዕሳቱ ላይ ይወርዳል፡፡ ከዚያም ሲቀዘቅዝ አይቡን ከአጓቱ ለይቶ ማጥለል፣ በማጥለያ ላይ አይቡን ከድኖ ማስቀመጥ፡፡ ይህም በአይቡ ውስጥ ያለው አጓት ተንጠፍጥፎ እንዲወጣ ያደርገል፡፡ በመቀጠል አስፈላጊ የሆኑ ውህዶች ቅመማቅመም፣ የተቀመመ ሚጥ ሚጣ፣ የተነጠረ ለጋ ቅቤ እና ትንሽ ጨው በተዘጋጀው አይብ ላይ በመቀላቀል ለምግብነት ይቀርባል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## የሙዚቃ መሳሪያዎች

**(የክፍለ ጊዜ ብዛት 12)**

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-**

- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በስዕል ተመልክተው ስማቸውን ይናገራሉ፡፡
- ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በስዕል ተመልክተው ስማቸውን ይናገራሉ፡፡
- የቀረበውን ግጥም በሚና ጨዋታ መልክ ይከውናሉ፡፡
- ጽሁፉን አንብበው ሀሳቡን ይገልጻሉ፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያዎችን አይነትና አዘገጃጀት ዘርዝረው ይጽፋሉ፡፡
- ሙዚቃ መሳሪያዎችን ከተግባራቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡

## ሀ.አዳምጦ መናገር

## አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት አንድ

### ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ስያሜዎችን አዳምጦ መናገር

- መምህር/ት፡- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉትን ስዕሎች እያሳዩ ሲያስረዱ በማዳመጥ ተማሪዎች የሙዚቃ መሳሪያውን ስያሜ በማስታዎስ መልስ ይሰጣሉ፡፡
- መምህር/ት እባክዎትን በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያለውን ስዕላዊ መግለጫ እያሳዩ ተማሪዎች የእያንዳንዱን ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ስያሜ በትክክል እንዲያውቁ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡
- መምህር/ት የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ስያሜን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡

| ተ.ቁ | ስዕል | ተ.ቁ | ስዕል |
|---|---|---|---|
| 1 | ጥሩንባ | 5 | ከበሮ |
| 2 | በገና | 6 | ክራር |
| 3 | መሰንቆ | 7 | ዋሽንት |
| 4 | አርሞኒካ | 8 | ጸናጽል |

መምህር/ት የቀረቡትን ስዕላዊ መግለጫ መሰረት በማድረግ ከጥያቄ ሀ እስከ ሰ ድረስ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን ምልስ በቃል እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

## ትምህርት ሁለት

### ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ ስያሜዎችን አዳምጦ መናገር

መምህር/ት በቀጥታ ወደ ክፍለ ትምህርቱ ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎች የሚያውቋቸው ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ካሉ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ይዘቱ ከመግባታቸው በፊት የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲያብሰለስሉ እንዲሁም ቀጥሎ የሚመጣው የትምህርት ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ዕድል ይሰጣል፡፡

■መምህር/ት እባክዎትን በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያሉትን ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ሰዕሎችን ለተማሪዎች በማሳየት የእያንዳንዱን ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስያሜያቸውን በመንገር ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎችም አርስዎ የሚሰጧቸውን ገለጻ በማዳመጥ የሙዚቃ መሳሪያውን ስያሜ ስም እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡ ይህ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ በጥቁሩ ሰሌዳ ላይ የእያንዳንዱን ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስያሜ ይጻፉላቸው፡፡ በመቀጠል የቀረቡትን ስዕሎች በአጽንኦት ተመልክተው መልመጃ አንድን እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡

## ትምህርት ሦስት፡-

### የእንኳን ደስ ያለህ የመልካም ምኞት መግለጫ

መምህር/ት፡- ተማሪዎች የሚያውቁት የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግሮች ካሉ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በአካባቢያቸው የሚጠቀሙትን የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግሮችን እንዲገልጹ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች በተነቃቃ መንፈስ ወደ ዋናው ትምህርት ይዘት እንዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡ በመቀጠል በጫክሶ እና በታጸኔ መካከል የተደረገውን የሀሳብ ልውውጥን መሰረት በማድረግ መልመጃ አንድን እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡

## ትምህርት አራት ፡--

### የክር እና የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎቸችን አዳምጦ መናገር

መምህር/ት፡- ተማሪዎች ወደ ክፍለ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የክርና የትንፋሽ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ካሉ በዝርዝር እንዲገልጹ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን እንዲጠቀሙ እና የንግግር ክሂላቸውንም ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንዲሆን ያስችላል፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡ መምህር/ት እባክዎትን ይህን መልመጃ ተማሪዎችን ሲያሰሩ በቅድሚያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡

## የኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች

- **የክር ሙዚቃ** መሳሪያዎች፡- እነዚህ መሳሪያዎች ድምጽ የሚሰጡት በንዝረት ነው፡፡

**በገና፡-** መንፈሳዊ ዜማዎችን ለማዜም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሳሪያ ነው፡፡

**ክራር፡-** ይህ የጅማት የሙዚቃ መሳሪያ ለአያሌ ዓመታት ለደስታ፣ ለትካዜ፣ ለፍቅርና ለቀረርቶ ስንጠቀምበት የቆየ መሳሪያ ነው፡፡

**መሲንቆ/ ማሲንቆ/፡-** በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኝ ጥንታዊ መሳሪያ ነው፡፡

**ዱል፡-** በጋምቤላ የሚገኝ የጅማት መሳሪያ ነው፡፡

- **የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች፡-**

  **ዋሽንት፡-** አብዛኛው ጊዜ እረኞች በሀገር ቤት ይገለገሉበታል፡፡ በተጨማሪም በመድረክ ላይ ለክራርና ለማሲንቆ ቅኝት በመስጠትና ዜማን በማጀብ ያገለግላል፡፡

  **እምቢልታ፡-** ሶስት ዓይነት እምቢልታዎች አሉ፡፡ ስማቸውም - ኡፍን፣ አውራና የማ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ለክብረበዓልና ወደ ጦር ሜዳ ለመሄድ ሰልፈኛ የሚነፋ አድማቂ መሳሪያ ነው፡፡

  **መለከት፡-** ቀደም ባለው ጊዜ ሰዎች ተሰብስበው የመንግስት አዋጅ እንዲሰሙ ትዕዛዝን መስጫ መሳሪያ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ነው፡፡

**ጨቻ ዘዬ፡-** በደቡብ ኢትዮጵያ ውዝዋዜ ለማድመቅ የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

❖ **የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች፡-**

**ከበሮ፡-** ለዘፈን ማድመቂያና ለሰርግ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ዝማሬ ቀሳውስት በሽብሸባ ጊዜ የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው፡፡

**አታሞ፡-** ለሙዚቃና ለጭፈራ የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

**ነጋሪት፡-** በሰልፍ ጊዜ በአንዳንድ ብሔረሰብ ለለቅሶ ማድመቅያነት የሚጠቀሙት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

**ጸናጽል፡-** ለመንፈሳዊ ዝማሬ ቀሳውስት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው፡፡

**ቅል፡-** ቅል በውስጡ ጠጠሮች ወይም ፍሬዎች ተጨምረውበት ለዘፈን ማድመቂያ ያገለግላል፡፡

## ትምህርት አምስት፡-

### የሚና ጨዋታ

ክራርና ከበሮን ተጠቅሞ ተግባራትን መከወን

■ መምህር/ት እያንዳንዱ ተማሪ በጥንድ ሆነው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተዜሙ ሀገር በቀል የሆኑ ግጥሞችን ተጠቅመው በክራርና በከበሮ አማካይነት በክፍል ውስጥ እንዲያዜሙ ያድርጉ፡፡ የክራርና ከበሮ አጠቃቀምንም ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡ መምህር/ት እባክዎትን ክራርንና ከበሮውን ከግጥሙ ዜማ ጋር አዋህደው በትክክል መከወን ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡ ይህም ተማሪዎች

የትምህርቱን ይዘት ወደውት እንዲማሩ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ክፍለ ትምህርት ትምህርቱ የሚቀርበው በሚና ጨዋታ በመሆኑ ትምህርቱ የሚቀርብበትን ቋንቋ በቀላሉ እንዲለምዱት ያስችላል፡፡ የንግግር ክሂላቸውንም እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም መምህር/ት ሌሎች ሀገር በቀል ዜማዎችን በተመሳሳይ ክፍለ ጊዜ ቢጠቀሙ ጥሩ አማራጭ ይሆናል፡፡

## ማንበብ

### ትምህርት ስድስት፡-

### ስያሜዎችን ማንበብ

የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን መሰረት ያደረጉ ቃላትን  በጥቁር ሰሌዳ ላይ ወይም ፍላሽ ካርዶችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ የሚያነቡትንም ተማሪዎች ያበረታቷቸው፡፡

መምህር/ት ሌሎችንም ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ስያሜዎችንም እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡ የንባቡ ዓላማ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ሀገራችን ውስጥ ያሉ ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አጥብቀው እንዲያውቁና የንባብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ነው፡፡

መምህር/ት እባክዎትን ተማሪዎች እያንዳንዱን ስያሜ በትክክል ስለማንበባቸው ያረጋግጡ፡፡

መምህር/ት፡- ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በሚል የቀረበውን ምንባብ በዝግታ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፤ በመቀጠልም ተራ በተራ የስነብቧቸው፡፡ የዚህ ክፍለ ትምህርት ዋነኛ አላማ የተማሪዎችን የንባብ እና የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ነው፡፡ ስለሆነም የእርስዎ ክትትል እና ድጋፍ የተማሪዎችን የንባብና የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አውቀው፤ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ በኢትዮጵያ ሀገራችን ምንምን ዓይነት ዓይነት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችአሉ? በማለት ይጠይቋቸው፡፡ይህም ተማሪዎች ምንባቡን ለማንበብ መነቃቃትን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በመቀጠልም ሁለቱን አንቀጽ ካነበቡ በኋላ ጊዜ ንባብ ላይ ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር አብረው መሆናቸውንና ትምህርቱን በሚገባ መከታተል ስለመቻላቸው ጥቆማ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም ምንባቡ ተነቦ ካለቀ በኋላ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡

መምህር/ት ምንባቡን የማስነበቡ /የትምህርቱ/ ዋነኛ አላማ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት አቅማቸውን ማጎልበት መቻል ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ትምህርት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ምንባቡን በትክክል ማንበብ ስለመቻላቸው ቅድመ ንባብ፣ ጊዜ ንባብ፣ ድህረ-ንባብ ጥያቄዎችን መስራት ስለመቻላቸው ይጠበቃል፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡

**መጻፍ**

**ትምህርት ሰባት፡-**

## ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን አይነትና አዘገጃጀት መጻፍ

- መምህር/ት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚያቁት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ጠይቀው እንዲጽፉ ያበረታቱ፡፡ የዚህ ትምህርት ክፍል ዋነኛ ዓለማ ተማሪዎች ነገሮችን በጽሁፍ መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡
- መምህር/ት አባክዎትን ተማሪዎች ስለከበሮ፣ጸናጽል፣ክራር እንዲሁም ዋሽንት አሰራር ቃላትን በተገቢው ቦታ አኑረው መጻፍ ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡
- መምህር/ት ተማሪዎች የቀረበውን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስያሜዎችን ተጠቅመው ተገቢውን ስያሜ በተገቢው ቦታ እንዲያሟሉ ያድርጓቸው፡፡ የዚህ ትምህርት ክፍል አላማ በጎደለው ቦታ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስያሜውን ተጠቅሞ የዐ.ነገሩ ሀሳብ የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም ስለቀረቡት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ግንዘቤ እንዲፈጥሩ ማድረግ ነው፡፡

**መርጃ መሣርያ**

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ሥዕሎች፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሣርያዎችን ለምሳሌ፡- የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አዘጋጅቶ በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ግምገማ**

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በመጠየቅ ማረጋገጥ፣ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን በማሰራት፣ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን እንዲያሚሉ በማድረግ፣ እና በመሳሰሉት መገምገም ይቻላል፡፡

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት፣ ሐረጋትን እና አረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ በማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፤

**በአጠቃላይ ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽን ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል።

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ ሰባት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥና የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ናቸው። ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም። ይሁን እንጂ በአዳምጦ መናገር ስር የቀረቡት ምስሎችን፣ ስሞችን አይነት በቁጥራቸው ልክ በትክክል እንዲጽፉ በማድረግ ማሰራት ይቻላል።

**አዳምጦ መናገር**

**ትምህርት አንድ**

**መልመጃ አንድ**

| | |
|---|---|
| ሀ | አርሞኒካ |
| ለ | ጥሩምባ፣ ዋሽንት |
| ሐ | ጥሩምባ |
| መ | ዋሽንት |
| ሠ | ክራር፣ በገና |
| ረ | መሰንቆ |
| | |

## ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. ጊታር
2. ሳክስፎን 3. ኪይ ቦርድ
4. ሳክስፎን ዘመናዊ የትንፋሽ መሳሪያ ነው፡፡ ቫዮሊን ግን የሙዚቃ መሳሪያው ላይ ባለው ክር አማካይነት ድምጹን የምንቀኝበት ነው፡፡

## ትምህርት አራት፡-

### መልመጃ አንድ

ሀ) 1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት

### መልመጃ ሁለት

1. ከበሮ ከምት የሚመደብ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡
2. ነጋሪት በሰልፍ ጊዜ በአንዳንድ ብሔረሰብ ለለቅሶ ማድመቅያነት የሚጠቀሙት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡
3. ሶስት ዓይነት እምቢልታዎች አሉ፡፡ ስማቸውም፡-

ኡፍን፣ አውራና የማ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ለክብረ በዓልና ወደ ጦር ሜዳ ለመሄድ ሰልፈኛ የሚነፋ አድማቂ መሳሪያ ነው፡፡

## ማንበብ

### ትምህርት ስድስት፡-

### መልመጃ አንድ

| ተ.ቁ | መልመጃ አንድ (መልስ) |
|---|---|
| 1 | ለ |
| 2 | ሀ |
| 3 | ሐ |
| 4 | ለ |
| 5 | ለ |
| 6 | ሀ |
| 7 | ለ |

## መጻፍ

### ትምህርት ሰባት፡-

| ተ.ቁ | መልመጃ ሁለት |
|---|---|
| 1 | ክራር |
| 2 | ከበሮ |
| 3 | መሰንቆ |
| 4 | ከበሮ |
| 5 | ዋሽንት |

## ምዕራፍ ስምንት

## ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎች

**(የክፍለ ጊዜ ብዛት 12)**

**የሚጠበቅ ውጤት፡-**

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- በሥዕላዊ መግለጫዎች ወይም በፎቶ ግራፍና የቀረቡላችሁን የባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታ ዓይነቶች ተመልክተው ይናገራሉ፡፡
- ባህላዊና ዘመናዊ የጨዋታ ዓይነቶችን በሚገልፁ ቃላት ሀረጎችና አረፍተ ነገሮችን መስርተው ያነባሉ፤ይጽፋሉ፡፡
- ባህላዊና ዘመናዊ የጨዋታ ዓይነቶችን የያዘ ጽሁፍ አንብበው ሀሳቡን ይገልጻሉ፡፡
- የዘመናዊ ጨዋታ ዓይነቶችን ዝርዝር አስተካክለው ያነባሉ፡፡ ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን አሟልተው ይፅፋሉ፡፡

**አዳምጦ መናገር**

**ትምህርት አንድ፡ -**

**ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎችን አተገባበር አዳማጦ መናገር**

መምህር/ት፡- ወደ ትምህርቱ ይዘት ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ባህላዊ የጨዋታ አይነቶች ካሉ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ይህም ቀጥሎ የሚመጣው የክፍለ ትምህርቱ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲያስቡ ያደርጋል፤ እንዲሁም መነቃቃትን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በመቀጠል የቀረበውን ምስል ተመልክተው መልመጃ አንድን በጥንድ በመሆን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ሁለት፡ -

### ባህላዊ ጨዋታ

መምህር/ት፡- በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ስለገበጣ መጫወቻ አስመልክቶ ያለውን ምንባብበዝግታ ያንብቡላቸው፡፡ ተማሪዎቹምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል ምንባቡን መሰረት አድርጎ የቀረበውን መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡

መምህር/ት፡- መልመጃ ሁለት ላይ በዝርዝር የቀረቡትን የጨዋታ አይነቶች መሰረት አድርገው በየምድቡ( ባህላዊ፣ ዘመናዊ) በማለት እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፤ ተማሪዎችን ያበረታቱ፡፡

## ትምህርት ሦስት

### የዘመናዊ ጨዋታ ስሞችን መናገር

መምህር/ት ወደ ክፍለ ትምህርቱ ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ወይም ከዚህ በፊት የሚያውቋቸው ዘመናዊ የዋታ አይነቶች ካሉ በዝርዝር እንዲገልጹ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡

1.ቼዝ

2.ፑል

3.ከረንቡላ

4.ሞባይል ላይ የሚገኝ ጨዋታ

**መፃፍ**

## ትምህር አራት፡ -

### የባህላዊ መጫወቻ መሳሪያዎችን መጻፍ

መምህር/ት፡- በቅድሚያ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ባህላዊ የጨዋታ አይነቶችን በዝርዝር እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል በአካባቢያው የሚከወኑ ባህላዊ ጨዋታዎችንና የጨዋታው ህግን እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ ይህም በተነቃቃ መንፈስ ወደ ክፍለ ትምህርቱ እንዲገቡ ያስችላል፡፡ ከዚያም በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ስለ ገና ባህላዊ ጨዋታ አስመልክቶ የቀረበውን ማስታወሻ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎች ግንዛቤ መፍጠራቸውን ካረጋገጡ በኂላ ምንያህል ግንዛቤ እንደያዙ ለማወቅ የቃል ጥያቄ ተማሪዎችን ይጠይቁ፡፡ ተማሪዎቹ ተገቢውን መልስ በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድን ያሰሯቸው፡፡

መምህር/ት፡- በዚሁ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የገና ባህላዊ ጨዋታን አስመልክቶ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት አድርገው መልመጃ ሁለት (አዛምድ)ን ተማሪዎች በግል ሆነው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ያበረታቷቸው፡፡

## ትምህርት አምስት

### ቃላት

መምህር/ት፡- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ ሁለት ትርጉም ስለሚሰጡ ቃላት፤ የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች አስመልክቶ ለተማሪዎች ጠቅለል ያለ ገለጻ ከምሳሌ ጋር ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል ቃላት ሲጠብቁ የሚኖራቸውን ፍች አስመልክቶ በመልመጃ አንድ ምድብ(ሀ) ስር የቀረበውን ተማሪዎች እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡ በማስከተል በ(ለ) ምድብ የቃላት ተመሳሳይ ፍችን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ትዕዛዝ በተመሳሳይ መልኩ በግል ሆነው እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት

### ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች መስጠት

መምህር/ት፡- ለተማሪዎች ስለ ቃላት ተመሳሳይ ፍች ግንዛቤ ከፈጠሩላቸው በኋላ በ(ሀ) ምድብ ለቀረቡት ቃላት በግል ሆነው ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ይርዷቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር/ት፡- በቅድሚያ ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ስለቃላት **ተቃራኒ ፍች** ምንነት ይጠይቋቸው፡፡ ይህም የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት የሚቀሰቅስ በመሆኑ ቀጥሎ ከሚመጣው ክፍለ ትምህርት ጋር የሚኖራቸው ትስስር የጠበቀ እንዲሆን ያስችላል፡፡ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፍዝ እንዳይሆን የሚረዳ በመሆኑ ለሁሉም ክፍለ ትምህርተ ጥቅም ላይ ተግባራዊ ቢያደርጉት ለውጡን እዚያው በፍጥነት ያዩታል፡፡ በመቀጠል በ(ለ) ምድብ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍችያቸውን በምሳሌው መሰረት እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

***መርጃ መሣርያ***

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ከነዚህም ውስጥ፡- ጥቂቶቹ *ሥዕሎች* ፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ከአንድ በላይ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የጨዋታ አይነቶችን በመርጃ መሣርያነት በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

***ግምገማ***

♣ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

♣ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት እንዲጽፉበማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

♣ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩማበረታቻዎችን መስጠት፤

**በአጠቃላይ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽን ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ ስምንት ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ ና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ምስሎችንና ምንባብን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ግን ቁርጥ ያለ ምላሽን የሚፈልጉ ናቸው፡፡

**ትምህርት ሁለት፡-**

**ባህላዊ ጨዋታ**

| ተ.ቁ | መልመጃ አንድ |
|---|---|
| 1 | ሐሰት |
| 2 | እውነት |
| 3 | እውነት |
| 4 | አውነት |
| | |

**መፃፍ**

## ትምህር አራት፡

**የባህላዊ መጫወቻ መሳሪያዎችን መጻፍ**

| ተ.ቁ | መልመጃ አንድ |
|---|---|
| 1 | ለ |
| 2 | ሀ |
| 3 | መ |
| 4 | ሀ |
| 5 | ሐ |

## ትምህርት አምስት

**ቃላት**

**መልመጃ አንድ**

| ተ.ቁ | ቃላት ሲጠብቁ የሚሰጡት ፍች |
|---|---|
| ሀ.1 | ታግባ፤ ጎጆ ትመስርት |
| 2 | ከሆነ ነገር ላይ ተሰብሮ የወደቀ |
| 3 | ተመገበ |
| 4 | ባህላዊ መጠጥ፤ ተጸየፈ |
| 5 | ክብረ በዓል |

## ትምህርት ስድስት

### መልመጃ አንድ

| ተ.ቁ | ሀ. የቃላት ተመሳሳይ ፍች |
|---|---|
| 1 | ተጓዘ |
| 2 | ተመገበ |
| 3 | ተመለከተ |
| 4 | እረፍት አደረገ |
| 5 | ፈለገ |

## ምዕራፍ ዘጠኝ

# አካባቢያችን

(የክፍለ ጊዜ ብዛት 12)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

**ተማሪዎች ፣ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

■አካባቢያችሁን በሚመለከት ለሚቀርብላችሁ ጥያቄዎች መልስ ይሠጣሉ፡፡

■አካባቢን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ሀሳብ ይለዋወጣሉ፡፡

■ምንባቡን አንብባችሁ መልመጃዎችን ይሰራሉ፡፡

■አካባቢን በሚመለከት የሚነበብላችሁን ጽሁፍ አዳምጠው መልዕክቱን ይጽፋሉ፡፡

■ስለአካባቢያችሁ አጠቃላይ ሁኔታ ይጽፋሉ፡፡

■የአካባቢ ብክለትን የሚያስከትሉ መንስኤዎችን በንግግርና በጽሁፍ ይገልጻሉ፡፡

■ የሰውነት ክፍሎችን ስያሜ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

■ ስለአካባቢያችሁ የሚገልጽ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

## አዳምጦ መናገር

**አንደኛ ሳምንት፡- ትምህርት አንድ**

### ስለ አካባቢያቸው ገጽታ አዳምጦ መናገር

▸ መምህር/ት አካባቢያቸውን በሚመለከት ለሚያቀርቡላችሁ ጥያቄዎች ተማሪዎች በቃል መልስ ይሰጣሉ፡፡

▸ መምህሩ/ርቷ የአካባቢያችንን ደህንነት በተመለከተ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመቀስቀስ ጥያቄዎች ቀርበዋል ፡፡ ሁሉም ተማሪ ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠት እንዲችሉ ያመቻቹላቸው፡፡

አካባቢያቸው ከብክለት የጸዳ እንዲሆን የሚያስችሉ ማብራሪያዎችን ከስዕላዊ መግለጫው ጋር እያነጻጸሩ ከሰጡ በኋላ ምንባቡን ያስነብቧቸው፡፡

### አካባቢ

አካባቢ ማለት በዙሪያችን ያለውን ነገር ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ይህም ሲባል የምንኖርበት መንደር፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልልና ኢትዮጵያ ሀገራችንን የሚያጠቃልል ሰፊ ገጽታ ያለው ነው፡፡ የአንዱ አካባቢ ገጽታ ጥሩ አለመሆን የሌለውንም አካባቢ ገጽታ ያበላሻል፡፡ በተቃራኒው የሌላው አካባቢ ገጽታ ውብና ማራኪ መሆን የሌላውንም አካባቢ ገጽታ ያማረ እንዲሆን ያስችላል፡፡

ለአካባቢው ተፈጥሯዊ ገጽታ የሚጨነቅ ሰው አካባቢው ላይ ያለውን ገጽታ በመንከባከብ ንጹህ፣ ከቆሻሻ የጸዳ መልካም ገጽታን የተላበሰ

እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ለዚህም ነው ሰው አካባቢውን ይመስላል የሚባለው፡፡

መምህር/ት፡- ከላይ የቀረበውን ምንባብ በዝግታ የንባብ ስልት ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ ተማሪዎች ስለአካባቢ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ካረጋገጡ በኋላ በክፍለ ትምህርት አንድ ስር አካባቢን መሰረት አድርጎ ከጥያቄ ቁጥር 1 እስከ 3 የቀረበውን ጥያቄ ጥንድ ሆነው በመወያየት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ሁለት

### ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ያለውን ፋይዳ መናገር

መምህር/ት እባክዎ፣በቅድሚያ በዚህ ክፍለ ትምህርት መነሻ ላይ የቀረበውን የማነቃቂያ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ይህም ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን የትምህርት ይዘት እንዲገምቱ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በዝግታ ካነበቡላቸው በኋላ በዚሁ መልመጃ ምድብ ሀ እና ለ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያመቻቹላቸው፡፡

### ሀ) ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ

ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ለሰው ልጅ ምቹ እና ለጤና አስተማማኝ ገጽታ ያለው ነው፡፡ የአየር ሁኔታው ነፋሻማ የሆነ፣ ከጫጫታ ድምጽ ነጻ የሆነ፣ በቂ የውሃ አቅርቦት ያለው፣ የመጸዳጃ አገልግሎትን የሚሰጥ፣ በአረንጓዴ ተክሎች የተሞላ፣ ከአየር ብክለት የጸዳ፣ እንዲሁም የደረቅና ፍሳሽ ማስወገጃ ያለው መሆን አለበት፡፡

### የአካባቢ ጽዳት

መኖሪያ ቤትን በየጊዜው ማጽዳት። መረማመጃ የሆነውን ወለል ጽዳቱን መጠበቅ፣መወልወል። የቤት ግድግዳውን በቁም መጥረጊያ መጥረግ፣ የተቀባው ቅብ ፕላስቲክ ቀለም ከሆነ ማጠብ እንዲሁም የሚታደስ አይነት ከሆነ ደግሞ ማደስ፣ መጠገን። የቤቱን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ክፍሉን ምንም አይነት ቆሻሻ እንዳይኖረው ማጽዳት ተገቢ ነው። በሥራ የተወጠረ አዕምሮ እረፍት እንዲያገኝ የምንኖርበት አካባቢ /ግቢ/ እይታችንን የሚስብ መሆን መቻል አለበት። ይህም አረንጓዴ ተክሎች ያሉበት፣ የሚያማምሩና ውብ የሆነ ገጽታ ያለው እንዲሆን ማድረግ።

መምህር/ት በቅድሚያ ከላይ የቀረበውን ምንባብ በሚገባያንብቡላቸው። ተማሪዎች ባዳመጡት ምንባብ መሠረት መልመጃውን መስራታቸውን ይከታተሉ።

## ትምህርት ሶስት

### የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለውን መንስኤ መናገር

መምህር/ት በቅድሚያ የአካባቢ ብክለትን በሚመለከት ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠልም በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያለውን ስዕላዊ መግለጫ በማሳየት ገለጻውን ያጠናክሩላቸው። ስዕላዊ መግለጫውን አስመልክቶ ግንዛቤ ስለመያዛቸው ያረጋግጡ።

ስዕላዊ መግለጫውን በትክክል መረዳት መቻላቸውን ይከታተሉ። ስዕላዊ መግለጫውን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ በቃል ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጓቸው።

## ትምህርት አራት፡-

### የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለው ችግር

መምህር/ት፡- ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት አካባቢያችንን ምን ምን ነገሮች ሊበክሉ እንደሚችሉ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ይህም በቀጥታ ከሚነበብላቸው ምንባብ ጋር ስለሚገናኝ የተወሰነ ግንዛቤ ፈጥረው ወደ ምንባቡ እንዲገቡ ያስችላል፡፡ በመቀጠል መልመጃ አንድን አስመልክቶ ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

### የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለው ችግር

የአካባቢ ብክለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት ወደ አካባቢ በሚለቀቅ ሙቀት የተነሳ በአካባቢያችን ያሉት የአየር፣ የውሃ፣ የአፈር አካላት ያላቸውን የተፈጥሮ ይዘት በመቀየር በሰው፣ በእንስሳትና በተክሎች ላይ ችግር ሲያስከትል ነው፡፡ እንዲሁም የመርዛማ ንጥረ ነገሮች ልቀት እንደ ካርቦን ሞኖ ኦክሳይድና ሰልፈር ዳይ ኦክሳይድ በአየር ውስጥ ያሉ እነዚህ ንጥረ ነገሮች በሰወነት ላይ ተጽዕኖ ሲያሳድሩና በጉሮሯችን ላይ የመተንፈስ ችግር ወይም አልፎ ተርፎም ስር የሰደደ የልብ በሽታዎችን ማስከተል ሲጀምር ነው፡፡

መምህር/ት ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ተማሪዎች መረዳት ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡ በመቀጠልም መልመጃ አንድ ላይ የቀረበውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፡-ትምህርት አምስት

### የአካባቢ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን መናገር

መምህር/ት በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ትምህርት አምስት ላይ የቀረበውን መረጃ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ገለጻውንም በሚገባ መረዳት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ በመቀጠልም መልመጃ አንድ ላይ የቀረበውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ በተጨማሪም ስዕላዊ መግለጫውን መሠረት ላደረገው ጥያቄ ምስሉን ተመልክተው ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንዲችሉ ይርዷቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት

### የተለያየ ገጽታ ያላቸውን አካባቢዎች ልዩነታቸውን በንጽጽር መናገር

መምህር/ት በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ስዕለዊ መግለጫ መሠረት አድርገው ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንዲችሉ ይርዷቸው፡፡ ተማሪዎቹ ስዕላዊ መግለጫውን ተንተርሰው ጥያቄውን መስራት ስለመቻላቸው ያረጋግጡ፡፡

**ማንበብ**

## ሶስተኛ ሳምንት፡-ትምህርት ሰባት

### አካባቢን የሚገልጽ ጽሁፍ ማንበብ

መምህር/ት በተማሪው መጽሀፍ "አካባቢን ከብክለት መጠበቅ" በሚል ርዕስ በተማሪ የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበውን ማስታወሻ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው ከዚያም ተማሪዎች ተራ በተራ ምንባቡን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር/ት ተማሪዎቹ የምንባቡን ይዘት በሚገባ መረዳታቸውን/መገንዘባቸውን/ ካረጋገጡ በኋላ ጥንድ ጥንድ ሆነው በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ከአካባቢያቸው ገጽታ ጋር በማነጻጸር ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

**መጻፍ**

## ትምህርት ስምንት

### ስለአካባቢ ገጽታ መጻፍ

መምህር/ት በቅድሚያ ስዕላዊ መግለጫውን አስመልክቶ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች የቀረበውን ስዕላዊ መግለጫ መሠረት በማድረግ ለጥያቄው በጽሁፍ ተገቢውን መልስ መስጠት እንዲችሉ ያድርጓቸው፡፡

መምህር/ት መልመጃ ሁለት ላይ የቀረበውን ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች አካባቢያቸውን የሚገልጽ አንድ ቀለል ያለ አንቀጽ እንዲጽፉ ይርዷቸው፡፡

## ትምህርት ዘጠኝ፡- ሰዋስው

### የሰውነት ክፍሎችን ስያሜ ተጠቅሞ አረፍተ ነገር መመስረት

መምህር/ት፡-ተማሪዎች የሰውነት ክፍሎችን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ ያበረታቱ፡፡ በትክክል የአረፍተ ነገር ቅርጽን አሟልተው የሚጽፉ ተማሪዎችን ያበረታቱ፡፡

## መርጃ መሣርያ

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ሥዕሎች ፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ስለአካባቢ ጽዳት፣ የአካባቢ ብክለት፣ የተጎዳ አካባቢ.፣ በረሃማ የሆነ አካባቢ፣ ጥሩ ገጽታ ያለው አካባቢ፣ የተበከለ ውሃ ፣ እና የመሳሰሉትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫዎችን በመርጃ መሣርያነት በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ግምገማ**

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በጠየቅ ማረጋገጥ፣

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት እንዲጽፉበማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመስጠት፤

**በአጠቃላይ፡-**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡

## ማሳሰቢያ፡-

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽን ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ ዘጠኝ ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥና የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ በአዳምጦ መናገር ስር የቀረቡትንምስሎች ተመልክተው ገለጻ እንዲያደርጉ በማድረግ፣ምስሎችን ተመልክተው እንዲጽፉ በማድረግ፣ ምንባብ አዳምጠው ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን በመስራት፣ ማስታወሻዎችን አዳምጠው እንዲገልጹ በማድረግ ማሰራት ይቻላል፡፡

**ማንበብ**

**ትምህርት ሰባት**

| ተ.ቁ | መልመጃ አንድ |
|---|---|
| 1 | እውነት |
| 2 | እውነት |
| 3 | እውነት |
| 4 | ሐሰት |

# ምዕራፍ አሥር

# ተረት

(የክፍለ ጊዜ ብዛት 10)

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ትምህርት በሚገባ ከተማሩ በኋላ፡-**

- ካዳመጡት ተረት የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ያነባሉ፣ ይጽፋሉ፡
- ተረት አዳምጠው የተረዱትን መልሰው ይናገራሉ፡፡
- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፣ ያነባሉ፡፡
- በተረት ውስጥ ያሉ ገጸባህሪያትን ለይተው ይናገራሉ፣ ይጽፋሉ፡፡

## አዳምጦ መናገር

### አንደኛ ሳምንት፡-ትምህርት አንድ

### ተረትን አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ

መምህር/ት ተረቱን ከማንበብዎ አስቀድመው ተማሪዎች ከዚህ በፊት የሚያስታውሱት ተረት ካለ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች በተነቃቃ መንፈስ ትምህርቱን እንዲከታተል ያስችላል፡፡ እንዲሁም በቀጣይ ስለሚማሩት የትምህርት ይዘት እንዲያስቡ ወይም እንዲገምቱ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

መምህር/ት እባክዎትን ከዚህ በታች የቀረበውን ተረት ለተማሪዎች በዝግታ ካነበቡላቸው በኋላ በተማሪ መጽሐጽፍ ላይ ያሉትን መልመጃዎች ያሰሯቸው፡፡

## ዛፎቹ

ከለታት አንድ ቀን በአለም ዙሪያ ያሉ ዛፎች ተሰብስበው ስለ ችግሮቻቸው ይወያዩ ነበር፡፡ ከመካከላቸው አንዱ እንዲህ አለ “የኛ ትልቁ ችግር የደን መመንጠር ነው፡፡ ይህም ድርጊት የሚፈጸምብን መጥረቢያ በተባለ መሣሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ጠላታችን የሆነውን መጥረቢያ ማጥፋት አለብን፡፡”

ብዙዎቹም በዚህ ሐሳብ ዙሪያ አስተያየት በመስጠት “መጥረቢያ ነው የሁልጊዜ የስቃያችን ምንጭ ይቆርጠንና ሲያሻው ለማገዶ አልያም ለቤት ዕቃ መስሪያ፤ እረ ምኑ ቅጡ! ስለዚህ አንድ መላ ፈልገን ይህንን ጠላታችንን ማጥፋት አለብን” ብለው መከሩ፡፡

አንድ ባሕርዛፍም እጁን አውጥቶ “ጠላታችን ግን መጥረቢያ አይመስለኝም፡፡” አለ፡፡

በዚህን ጊዜ ሁሉም ዛፎች ወደ እርሱ ዞረው እንዴ! ምን ማለትህ ነው? እሱ ካልሆነ ታዲያ ማን ሊሆን ይችላል? ብለው ጮሁበት፡፡

ባሕርዛፉም ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ፡፡ “አያችሁ እኔ ከልቤ ነው የምላችሁ፡፡ ጠላታችን መጥረቢያ አይደለም፡፡ እኛው እራሳችን ነን ሁላችንም መጣመም ትተን ቀጥ ብለን ብናድግ ኖሮ መጥረቢያ እጀታ አይኖረውም፤ እኛም ከመቆረጥ እንድን ነበር፡፡

ስለዚህ ከዚህ በኋላ ሁላችንም ሳንጣመም ቀጥ ብለን በማደግ የመጥረቢያውን እጀታ ማሳሳት አለብን፡፡” በዚህ ጊዜ ሁሉም ዛፎች አጨበጨቡለት፡፡

(ኢቶጺስ ፡፡ የልጆች ተረት ፣ ገጽ 10)

## ትምርት ሁለት

### ከተረት አዳዲስ ቃላትን ለይቶ ማውጣት

መምህር/ት፡- ከዚህ በታች የቀረበውን ተረት ለተማሪዎች ሁለት ግዜ ካነበቡላቸው በኋላ በተማሪው መጽሐፍ ላይ ያሉትን መልመጃዎች እንዲሰሩ ይርዷቸው፡፡

<u>**ጅብና እንቦሳ**</u>

ከዕለታት አንድ ቀን ከብት አርቢ፣ ዘላን ላሙ መውለዷን ሳያይ የወለደችውን ላም ጥሎ መሸት ሲል ከብቶቹን ነድቶ ወደ በረት ወሰዳቸው፡፡ የወሰዳቸው ላምም ከመንጋዋ ተነጥላ በመቅረቷ ተከትላ ለመሄድ ፈለገች፡፡ ግን በአንድ ልቧ እንቦሳዋን ጥላት እንዳትሄድ በጣም ጨነቃት፡፡ መንጋዋ ወደ ሄደበት ትራመድና እንደገና እንቦሳዋን፣ ልጇን እየዞረች ታያለች፡፡ እንቦሳዋ ግን ልትከተላት አልቻለችም፡፡ እንዲህ ስትል እየጨለመ ሄደ፡፡ በኋላ ላሚቷ ጨክና መንጋዋ የሄደበትን መንገድ ተከትላ ወደ በረቷ አመራች፡፡ እንቦሳዋ ስን ብቻዋን ቀርታ ሳለች ጅብ ምግብ ፍለጋ እያፎነፎነ እንቦሳይቱ ካለችበት ድረስ ከች አለ፡፡ በዚህ ጊዜ እንቦሳዋ በጣም እርቧት ስለነበርና እናቷ ስለመሰላት ወደ ጅቡ እየሮጠች ተጠጋች፡፡ በዚህ ጊዜ ጅቡ ደነገጠና አይኑን እያብለጨለጨ በፍርሀት ቆሞ ተመለከታት፡፡ እንቦሳይቱ ግን ይበልጥ እየቀረበት መጣችበት፡፡ በዚህ ጊዜ ጅቡ በድንጋጤ ዞሮ እሩጫውን ቀጠለ፡፡ እንቦሳይቱም እናቴ አመለጠችን በሚል ከኋላው እየፈረጠጠች ተከተለችው፡፡ ወዲያው ጅቡ ሲሮጥ እምቦሳዋ እንዲሁ ስትሮጥ ጅቡ በጣም ደከመ፡፡ በኋላም ልቡ ድልቅ

ድልቅ እያለ እየመታ፣ እንባው እየተወተፈ፣ ጉልበቱ ሁሉ እየተሳሰረ መራመድ ተሳነውና ዘፍ ብሎ ወድቆ በፍርሃት ተኛ፡፡ እምቦሳዋም ከአጠገቡ ቆማ ከአሁን አሁን ተነስታ ጡቷን በጠባሁ እያለች ስትጠብቅ ለሊቱ ተወገደና ነጋ፡፡ በለሊት ጦሩን ይዞ እንቦሳይቱን ይፈልግ የነበረው እረኛ ደክሞት በረሃብና በድካም የተኛውን ጅብ እና እንቦሳዋን አገኘ፡፡ በመጨረሻም ጅቡን በጦር ወግቶ እንቦሳውን ይዞ ወደ በረቱ መጣ ይባላል፡፡

(ባይለኝ ጣሰው፣ የአችዋ ተረቶች፣ ሌሮዋች አችዋ፣ በ1995 አ.አ) ለተማሪዎቹ እንደሚስማማ ተደርጎ ተሻሽሎ የቀረበ

**ማንበብ**

## ትምህርት ሶስት

### ከሚነበብ ተረት የአዳዲስ ቃላትን አገባብ መረዳት

መምህር/ት በዚህ ክፍል ከተረቱ ውስጥ አዳዲስ የሚሏቸውን ቃላት እያስታወሱ እንዲጠሩ ያድርጓቸው፡፡ ቃላቱን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ የቃላቱን ፍቺ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠል በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች ያሰሯቸው፡፡

### መጻፍ

## ትምህርት አራት

### ሰነፍ ተማሪ

በዚህ ክፍል አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ተረቱን ተማሪዎቹ ረጋ ብለው እንዲያነቡ ነግረው እኩል ያስጀምሯቸው፡፡ በየጎናቸው ከተቀመጡ ተማሪዎች ጋር እየተጎነታተሉ ወይም እያወሩ በተመስጦ ማንበቡን እንዳይተው ክፍል ውስጥ እየተዟዟሩ ይቆጣጠሯቸው፡፡

አንብበው ሲጨርሱ ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡ እንዲሁም ከተረቱ የወጡትን ቃላትና ዓ.ነገር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

ደጋግመው እንዲጽፉ የተጠየቋቸውን አረፍተ ነገሮችደጋግመው መጻፋቸውንና እጅ ጽሁፋቸው መሻሻሉን ያረጋግጡ፡፡

ይህ ክፍል ተማሪዎቹ ከቃላት ጀምሮ አረፍተ ነገሮችንና አንቀጾችን ከራሳቸው እያመነጩ የሚጽፉበት ክፍል ነው፡፡ ይህን መተግበር መቻላቸውን በክትትል ያረጋግጡ፡፡

**መርጃ መሣርያ**

በቋንቋ ትምህርት ሂደት መርጃ ማሣሪያነት የሚያገለግሉ ብዙ አማራጮች ቢኖሩም ጥቂቶቹ ሥዕሎች፣ ግራፎችና የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዕለቱ ትምህርት ይዘት ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ከአንድ በላይ መርጃ መሣርያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን በማዝናናት ትምህርቱን ወደውት እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ግምገማ**

▸ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ጽሁፍ ምን ያህሉን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ በጠየቅ ማረጋገጥ፡፡

▸ተማሪዎች ከምዕራፉ ውስጥ የተማሯቸውን ሆሄያት፣ ቃላት እንዲጽፉበማድረግ መገምገም፤ እየተከታተሉ ጽህፈታቸውን ማስተካከል፤

▸ተማሪዎች ቋንቋውን በጨዋታ መልክ አዘውትረው እንዲገለገሉበት የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፤

**በአጠቃላይ**

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውና በሚማሩት ቋንቋ መካከል ባለው ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ የድምጽን ንበት ስህተቶችን በበጎ ጎናቸው ማየት፤ ተፈጥሯዊ መሆኑን መረዳትና ማድነቅ ያስፈልጋል፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ መልሶች**

በምዕራፍ አስር ስር የቀረቡት መልመጃዎች አብዛኛዎቹ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ ና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ እንዲኖራቸው አይጠበቅም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ምንባብን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ግን ቁርጥ ያለ ምላሽን የሚፈልጉ ናቸው፡፡

**ሀ. አዳምጦ መናገር**

**ትምህርት አንድ**

| ተ.ቁ | መልመጃ አንድ |
|---|---|
| 1 | በአለም ዙሪያ ያሉ ዛፎች |
| 2 | የደን መመንጠር |
| 3 | ባህር ዛፍ |
| 4 | ባህር ዛፍ |
| 5 | ዛፎች |

## ትምህርት ሁለት

**ሀ)ከተረት ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ለይቶ ማውጣት**

| ተ.ቁ | ዛፎቹ ከሚለው ተረት ውስጥ የወጡ አዳዲስ ቃላት |
|---|---|
| 1 | ዘላን |
| 2 | እንቦሳ |
| 3 | መንጋ |
| 4 | እያፎነፎነ |
| 5 | ከች አለ |
| 6 | ድልቅ፣ ድልቅ |

ለ)1.ሐሰት

2.ሐሰት

3.ሐሰት

4.እውነት

# ዋቢዎች

ሙሉጌታ ይታየው፡፡ (2008)፡፡ የ4ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የመምህር መምሪያ፡፡

ባይለኝ ጣሰው፡፡ (1995)፡፡ የአኝዋክ ተረቶች፣ ሌሮዋች አችዋ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

በደ.ብ.ብ.ሕ. ክልላዊ መንግስት የብሔረሰቦች ምክር ቤት አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ እና የጋሞ ጎፋ ዞን ባህል፣ ቱሪዚም እና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን መምርያ፣ ገጽ 220፣ ግንቦት 2008ዓ.ም፣ ሀዋሳ፡፡

ኢቶጲስ፡፡ የልጆች ተረት፣ ገጽ 10፡፡

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ለአራተኛ ክፍል

## የተዘጋጀ (2014ዓ.ም)

| ርዕስ | የሚጠበቅውጤት/out come/ | ይዘት | የመማር ማስተማር ክንውን | ምዘና | ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| ማ | ሆሄያትንና ቃላትን አዳምጠው በትክክል ይጠራሉ | የሆሄያትና የቃላት አጠራር | ሆሄያትንና ቃላትን አዳምጠው በትክክል እንድጠሩ ማድረግ | የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች | 3 |
| ዳ<br>መ | ዲቃላ ሆሄያትንና ቃላትን አዳምጠው መልሰው በትክክል ይናገራሉ | የዲቃላ ሆሄያት ንበት | ቃላትን እንዲሁም ዲቃላ ሆሄያትን የያዙ ሀረጎችን በማንበብ አዳምጠው በትክክል እንዲያነቡ ማድረግ | የቃል ጥያቄ | 2 |
| | ሀረጎችን አዳምጠው ጥያቄዎችንይመልሳሉ፡፡ | የሀረጎች አጠራር | ሀረጎችን በማንበብ ለጥያቄዎች በቃል መልስ እንዲሰጡ ማነሳሳት | የቃል ጥያቄና መልስ | 3 |
| ጥ | አረፍተ ነገሮች ሲነበቡ አዳምጠው ደግመው ይናገራሉ፡፡ | አረፍተ ነገሮችን አዳምጦ መልሶ መናገር | የተቀረጹ/በጽሁፍ/ የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን በማስደመጥ መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ | የቃል ጥያቄ | 3 |
| | መመሪያዎችን ተከትለው ትዕዛዞችን ይተገብራሉ፡፡ | መመሪያዎችን መተግበር | የተለያዩ መመሪያዎችን ተከትለው ትዕዛዞችን እንዲተገብሩ ማድረግ | ምልከታ | 2 |
| | ተረቶችን አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ፡፡ | ተረቶችን አዳምጦ መልሶ መናገር | የተለያዩ አጫጭር ተረቶችን አዘጋጅቶ ክፍል ውስጥ በማንበብ መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ | የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች | 4 |
| | ሥዕላዊ መግለጫዎችን ተመልክተው ማብራሪያ ይሰጣሉ | በሥዕላዊ መግለጫዎች የተመሰረተ ማብራሪያ መስጠት | ጥንድ ጥንድ ሆነው ሥዕላዊ መግለጫዎችን ተመልክተው እንዲወያዩና ስለ ሥዕሉ ማብራሪያ እንዲሰጣጡ መድረግ | ምልከታ | 6 |
| መ | በንግግር ሂደት ሆሄያትንና ቃላትን በተገቢው ሁኔታና በትክክል ተጠቅመው ይናገራሉ ፡፡ | የሆሄያትና የቃላት አጠራር | የተቀረጹ ንግግሮችን በማቅረብ /በጽሁፍ/ መምህሩ ያዘጋጀውን ሆሄያትና ቃላት | | 4 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ና<br>ገ<br>ር | | | በማስደመጥ መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ | | |
| | የእንኳን ደስ አለህና የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግሮችን ይጠቀማሉ | የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግሮች | የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግሮችንና | የቃል እርማት | 3 |
| | መምህሩ በሚሰጣቸው አጫጭር ታሪኮች መነሻነት ተለማምደው በክፍል ውስጥ በንግግር ያቀርባሉ | ሚና ጨዋታ | በሚናጨዋታዘዴበክፍልው ስጥእንዲተገብሩ ማመቻቸት | ምልከታና እርማት ቤትወሰድ ስራ | 4 |
| | የቤትና የዱር እንስሳትንሥዕል ተመልክተው ሰው ላይ አደጋ የሚያደርሱትንና የማያደርሱትን ከነ ባህሪያቸው ይናገራሉ | ሥእላዊ መግለጫዎች | የቤትና የዱር እንስሳትንሥዕሎች በማሳየት ሰው ላይ አደጋ የሚያደርሱትንና የማያደርሱትን ከነ መከላከያ ዘዴያቸው ንዲናገሩ ማድረግ | የቃል ጥያቄ | 6 |
| | ተረቶችን ሲነበብ አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ | ተረቶች | የተለያዩ አጫጭር ተረቶችን አንብበው ወይም አዳምጠው መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ | የቃል ምዘና | 4 |
| | ♣ስለሚያውቁት የምግብ አሰራር ክፍል ውስጥ ገለጻ ያደርጋሉ | ንግግር | ♣ስለሚያውቁት የምግብ አሰራር ክፍል ውስጥ ገለጻ እንዲያደርጉ ማድረግ | የቃል ጥያቄ<br>ውይይት | 2 |
| ማ<br>ን | የተለያዩ ነጠላና ድርብ ሆሄያትን በትክክለኛ ንበት ያነባሉ | የሆሄያት ንበት | የተለያዩ ነጠላና ድርብ ሆሄያትን የያዘ ጽሁፍ ለተማሪዎቹ በማደል በትክክለኛ ንበት እንዲያነቡ ማድረግ | በማዳመጥ ማረም | 2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በ | ♣ ✔ሀረጎችን ያነባሉ | ✔ሀረጎች | ♣በቃላት ሀረግ መስርተው እንዲያነቡ ማድረግ | | |
| | የተለያዩ ስሞችን ያነባሉ | የአልባሳት፣የእ ንስሳትና ሌሎች ተዛማጅ ስሞች | የተለያዩ ነገሮችን ስያሜ የተለያዩ ሥእላዊ መግለጫዎችን እያሳዩ በገለጻ ዘዴ ማስተማር | የንባብ ምዘና | 5 |
| | ነጠላ ዐረፍተ ነገሮችንያነባሉ | ነጠላ ዐረፍተነገሮችን ማንበብ | ቀለልያሉዐ.ነገሮችንበማቅረ ብ የንባብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ | አቀላጥፎ ንባብ ምዘና | 5 |
| ብ | መጠይቃዊ(WH Question) ቃላትን(መቼ፣የት፣እንዴት… ) ለሚሉት ጥያቄዎችተገቢውን መልስ ይሰጣሉ | መጠይቃዊ ቃላት | መጠይቃዊቃላትንአዘጋጅቶ በጥያቄናመልስዘዴአንብበ ውምላሽእንዲሰጡማድረግ | አጭርመ ልስየሚሹ ጥያቄዎች | 2 |
| | የተዘበራረቁ ዐ.ነገሮችን በማስተካከል ወደአንቀጽ ቀይረው ያነባሉ | የተዘበራረቁ ዐ.ነገሮች | አንድን ክንውን የሚገልጹ ዐ.ነገሮችን አዘበራርቆ በማስቀመጥ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የተስተካከለ አንቀጽ እንዲመሰርቱ ማድረግ | የሙከራ ፈተና | 2 |
| | ተረቶችን ያነባሉ | ተረቶችን ማንበብ | ካነበቡት ተረት ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲመልሱ ማድረግ | አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች | 5 |
| መ ጻ | የተለያዩ ነጠላና ድርብ ሆሄያትን ይጽፋሉ | ሆሄያትን መጻፍ | የተለያዩ ነጠላና ድርብ ሆሄያትን የያዘ ጽሁፍ ለተማሪዎቹ በማደል ወይም በቃል በማጻፍ በትክክል መፃፍ መቻላቸውን መከታተል | የጽሁፍ ምዘና | 2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፍ | | | | | |
| | ቀላልና ተዘውታሪ ቃላትን ይጽፋሉ | ቃላትን መጻፍ | ስዕሎችንበማየትቃላትንእን ዲጽፉማድረግ | ምልከታ | 3 |
| | የቃላትንና የሐረጎችን ፍችያዛምዳሉ | ማዛመድ | የቃላትንናየሐረጋትንፍችእ ንዲያዛምዱማድረግ | የጽሁፍፈ ተና | 1 |
| | ያልተሟሉቃላትን በዲቃላ ሆሄያትአሟልተው ይጽፋሉ | ቃላትንአሟልቶ መጻፍ | ያልተሟሉ(ዲቃላ) ሆሄያትንአሟልተው ቃል እንዲመሰርቱ ማድረግ | የጽሁፍ ፈተና | 3 |
| | ሀረጎችን ይጽፋሉ | ሀረጎችን መጻፍ | ቃላትን አዘጋጅቶ በማቅረብ ሀረግ መስርተው መጻፋቸውን መከታታል | ምልከታ | 2 |
| | ተራ ዐ.ነገሮችን ይጽፋሉ | ተራ ዐ.ነገሮችን መጻፍ | ዐ.ነገሮችን ከራሳቸው አፍልቀው እንዲጽፉ ማድረግ | የጽሁፍ ምዘና | 3 |
| | የራሳቸውን ስምና ዕድሜ፣ የተወለዱበትን ጊዜና የሚገኙበትን አካባቢ በጽሁፍ ይገልጻሉ | ስለራሳቸውናስ ለአካባቢያቸው መጻፍ | ርዕስ በመስጠት ስለራሳቸውና ስለአካባቢያቸው እንዲጽፉ ማድረግ | የጽሁፍ ምዘና | 2 |
| | የሚያውቋቸውን አጫጭር ተረቶች ይጽፋሉ | ተረት መጻፍ | በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን አጫጭር ተረቶች ጽፈው እንዲያመጡ ማድረግ | የቤት ስራ | 4 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቃ<br>ላ<br>ት | የቤትናየዱርእንስሳትን ስሞችመጻፍ | የቤትናየዱርእ ንስሳ ስሞች | የቤትናየዱርእንስሳስዕሎች ንበማቅረብየስዕሎቹን ስማቸውንእንዲጽፉ ማድረግ | የጽሁፍ ጥያቄዎች | 5 |
| | ባህላዊናዘመናዊአልባሳ ትንስያሜዎች ይናገራሉ | የአልባሳት ስያ ሜዎች | በስዕልየተደገፉዘመናዊናባህ ላዊአልባሳትን ስሞች ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ | የቃልጥያቄዎች | 5 |
| | ባህላዊ የቤት ውስጥ መገልገያዎችንናጥቅማ ቸውንይዘረዝራሉ | ባህላዊ የቤት ውስጥ መገልገያዎች | የተለያዩባህላዊመገልገያዕቃ ዎችንስያሜናአገልግሎታቸ ውንእንዲናገሩማድረግ | የጽሁፍና የቃል ጥያቄ | 4 |
| | ባህላዊናዘመናዊየሙዚ ቃመሳሪያዓይነትና ጥቅም ይናገራሉ | የሙዚቃ መሳሪያዎች | ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በስዕል አስደግፎ በማቅረብ አይነትና ጥቅሙን እንዲናገሩ ማድረግ | ምልከታና ክትትል | 5 |
| | ✔የምግብ አይነቶችንና አዘገጃጀታቸውን በቅደም ተከተልይገልጻሉ | ✔የምግብ አይነቶችና አዘገጃጀት | የተለያዩ የምግብ አይነቶችንና አዘገጃጀትን በጽሁፍ እንዲገልጹ ማድረግ | የጽሁፍ ምዘና | |
| | ባህላዊናዘመናዊየጫወ ታአይነቶችን አተገባበር ይናገራሉ | የጫወታዎች አተገባበር | ባህላዊና ዘመናዊ የጨወታ አተገባበር ምሳሌ በማሳየት ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት እንዲተገብሩ ማድረግ | ቤት ወሰድ ስራ የጽሁፍጥያቄ የቃልጥያቄ | 4 |
| ስ<br>ዋ<br>ስ | ነጠላና ብዙ ቁጥር የሚያመለክቱ ተውላጠስሞችንይለያ ሉ | ተውላጠስሞች | ተውላጠስሞች ችን በመግለጽ ዐ.ነገር እንዲሰሩበትማድረግ | የጽሁፍ ጥያቄዎች | 2 |
| | በነጠላናብዙቁጥርአመ ልካችተውላጠስሞች አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ | አረፍተ ነገር መመስረት | ስለነጠላናብዙቁጥርአመልካ ችተውላጠስሞችበመግለጽ በተውላጣ ስሞቹ አረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግ | የጽሁፍጥያቄ | 2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ው | በታላሚው ቋንቋ ቀላልና የተሟሉ ዐ.ነገሮችን በተውላጠ ስሞችይመሰርታሉ | ተራዐ.ነገር | ስለተራዐ.ነገርበመግለጽና ምሳሌ በመስጠት ተራዐ.ነገር በተውላጠስሞች እንዲመሰርቱ ማድረግ | የጽሁፍጥያቄ | 2 |